የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ-ትምህርት

# የቃላት ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ

## በደቡብ ክልል በጉራጌ ዞን በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው አዲሱ የ6ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ተተኳሪነት

በ

እሙነሽ ኢላላ

ሰኔ 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የቃላት ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ

# በደቡብ ክልል በጉራጌ ዞን በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው አዲሱ የ6ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ተተኳሪነት

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ-ትምህርት

በተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን ማስተማር ለአርትስ ማስተር ዲግሪ ማሟያነት
የቀረበ ጥናት

በ

እሙነሽ ኢላላ

አማካሪ፡- ግርማ መንግስቱ (ዶ/ር)

ሰኔ 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ-ትምህርት


# የቃላት ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ

# በደቡብ ክልል በጉራጌ ዞን በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው አዲሱ የ6ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ተተኳሪነት


በ

እሙነሽ ኢላላ


የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ ---------------------------------- ፊርማ ----------- ቀን --------------------

የውስጥ ፈታኝ ---------------------------- ፊርማ ----------- ቀን --------------------

የውጭ ፈታኝ ---------------------------- ፊርማ ----------- ቀን --------------------

// ምስጋና

በመጀመሪያ ለዚህ ደረጃ ያደረሰኝ ልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይጋባው፡፡ በመቀጠል ከትልመ-ጥናቱ ጀምሮ እስከ መጨረሻው ፅሁፍ ድረስ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በአካልም ሆነ በስልክ ስህተቶቼን እያረሙ፣ እያበረታቱና ሙሁራዊ አስተያት እየሰጡ ጥናቴ ለዚህ ደረጃ እንዲበቃ ላገዙኝ አማካሪዬ ለዶ/ር ግርማ መንግስቱ ምስጋናዬ ከታላቅ አክብሮት ጋር ይድረስልኝ፡፡

የነጻ ትምህርት እድል በማመቻቸት አስተምሮ ይህንን ምርምር /ጥናት /እንዳካሂድ የገንዘብ ድጋፍ ጭምር ላደረገልኝ አንጋፋውን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

ለጥናቴ መሳካት ያለመሰልቸት አስፈላጊውን መረጃ በመስጠት የተባበራችሁኝ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቤተመጻህፍት ሰራተኞች ምስጋናየ ከፍ ያለ ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ ሥራ እንዲሳካ የማቴሪያል ድጋፍ ያደረጋችሁልኝ ሱተን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትቤት አስተዳደር ሰራተኞች፣ ውድ ጊዜያችሁን ሳትሰስቱ ለጥናቱ ጠቃሚ መረጃ በመስጠት ለተባበራችሁኝ መምህራን በሙሉ ያለ እናንተ ድጋፍ ይህ ጥናት ውጤታማ አይሆንም ነበርና ላደረጋችሁልኝ ቅን ትብብር ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

# አህፅሮተ ጥናት

*የዚህ ጥናት ዋና አላማ የቃላት ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ በደቡብ ክልል በጉራጌ ዞን በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው አዲሱ የ6ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ተተኳሪነት፡፡ ይህንንም አላማ ከግብ ለማድረስ ጥናቱ የተከተለው ገላጭ የምርምር ዘዴን ነው፡፡ ጥናቱን ከግብ ለማድረስም የተለያዩ ምሁራን ስለቃላት ትምህርት ይዘት አደረጃጀትና አቀራረብ ባነሷቸው ንድፈ ሀሳባዊ መስፈርቶችና መርሆዎች ላይ በመመርኮዝ በመማሪያ መጽሀፉ ላይ የሠነድ ፍተሻ በማድረግ እንዲሁም ለመጽሀፉ አዘጋጅና ለመምህራን ቃለ-መጠይቅ በማድረግ አስፈላጊው መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በመቀጠልም ከሰነድ ፍተሻና ከቃለ መጠይቅ የተገኙትን መረጃዎች በአይነት በአይነት በመመደብ የመተንተን ስራው ተከናውኗል፡፡*

*የትንተናው ውጤትም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትን በተመለከተ በጥሩ ሁኔታ የተደራጁ መሆናቸው፤ የቃላት ትምህርት አቀራረብን በተመለከተ በፍች ዝምድና ከማቅረብ አንጻር በመማሪያ መጽሑ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ተግባራት አቀራረብ ችግር ያለበት መሆኑ፤ በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ከማቅረብ አኳያ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ በመዝገበ ቃል በመደገፍ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች በቁጥር አነስተኛ ከመሆናቸውም በላይ በግልጽ መመሪያ አለመቅረባቸው ክፍተት መሆኑ፤ ግልፅ በሆኑ መመሪያዎች ከማቅረብ አኳያ መጽሀፉ  የቃላት ትምህርት ይዘት ተግባራትን በግልጽ መመሪያዎችና ምሳሌዎች የማቅረብ ክፍተት ያለበት መሆኑ በድክመት ተነስቷል፡፡*

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ


ምዕራፍ አንድ፣ መግቢያ ----------------------------------------------------------------------------1

1.1 የጥናቱ ዳራ -------------------------------------------------------------------------------------1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት------------------------------------------------------------------ 3

1.3 የጥናቱ አላማ-------------------------------------------------------------------------------------4

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ---------------------------------------------------------------------------------4

1.5 የጥናቱ ወሰን--------------------------------------------------------------------------------------- 4

1.6 የቁልፍ ቃላት ትርጓሜ -------------------------------------------------------------------------4

1.7 የጥናቱ ውስንነት------------------------------------------------------------------------------------5

ምዕራፍ ሁለት፣ ክለሳ ድርሳናት------------------------------------------------------------------ 6

2.1 የቃላት ምንነት------------------------------------------------------------------------------------ 6

2.2 የቃላት ትምህርት ምንነት ---------------------------------------------------------------------7

2.3 የቃላት ትምህርት አስፈላጊነት--------------------------------------------------------------- 7

2.4 የቃላት ትምህርት ይዘት ----------------------------------------------------------------------- 8

2.5 የቃላት ትምህርት አደረጃጀት ----------------------------------------------------------- 8

2.5.1 ቃላትን በቅርፅ ማደራጀት-------------------------------------------------------------------9

2.5.2 ቃላትን በሚያነሱት ርዕስ ጉዳይ ማደራጀት---------------------------------------------------9

2.5.3 ቃላትን በፍቺ ዝምድናቸው ማደራጀት---------------------------------------------------- 9

2.6 የቃላት ትምህርት ይዘቶች ማቅረቢያ መንገዶች-------------------------------------------- 11

2.6.1 ቃላትን በአውድ ማቅረብ---------------------------------------------------------------------- 12

2.6.2 ቃላትን በፍቺ ዝምድናቸው ማቅረብ--------------------------------------------------------- 12

2.6.2.1 ቃላትን በተመሳሳይ ፍቺ ማቅረብ ---------------------------------------------------- 13

2.6.2.2 ቃላትን በተቃራኒ ፍቺ ማቅረብ ------------------------------------------------------- 13

2.6.2. 3 የቃላት የማጠቃለልና የመዘርዘር ሁኔታ------------------------------------------------ 14
2.6.2.4 የቃላት አብሮ ተሰላፊነት---------------------------------------------------------------------- 14
2.6.3 ቃላትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ-------------------------------------------------------15
2.6.4 የቃላት ትምህርትን ግልፅ በሆኑ መመሪያዎች ማቅረብ ----------------------------------- 15
2.6.5 ቃላትን ከክሂል ትምህርቶች ጋር በማጣመር ማቅረብ-----------------------------------------15
2.7 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ------------------------------------------------------------------------- 17
ምዕራፍ ሦስት የአጠናን ዘዴ-----------------------------------------------------------------------------17
3.1 የጥናቱ ንድፍ ----------------------------------------------------------------------------------- 17
3.2 የመረጃ ምንጮች ---------------------------------------------------------------------------------17
3.3 የናሙና አመራረጥ-------------------------------------------------------------------------------------17
3.3.1 የመማሪያ መጽሀፍ ናሙና አመራረጥ--------------------------------------------------------17
3.3.2 የመምህራን እና የመጽሐፉ አዘጋጆች ናሙና አመራረጥ -------------------------------- 18
3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች -------------------------------------------------------------- 18
3.4.1 የሰነድ ፍተሻ --------------------------------------------------------------------------------------- 18
3.4.2 ቃለ-መጠይቅ ------------------------------------------------------------------------------------ 18
3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ-------------------------------------------------------------------------------- 18
ምዕራፍ አራት፣ የውጤት ትንተና -------------------------------------------------------------------19
4.1 የመጽሀፉ አጠቃላይ ዳራ -------------------------------------------------------------------------19
4.2 በመማሪያ መጽሀፉ የቀረቡ አጠቃላይ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች መረጃ --------------------19
4.3 በመማሪያ መጽሀፉ የተካተቱት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ምን ይመስላል?---22
4.4 በመማሪያ መጽሀፉ የተካተቱት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ምን ይመስላል?-----25
4.4.1 ቃላትን በአውድ ማቅረብ ------------------------------------------------------------------ 25
4.4.2 ቃላትን በፍች ዝምድና ማቅረብ ----------------------------------------------------------- 28
4.4.3 ቃላትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ ------------------------------------------------- 31
4.4.4 ቃላትን ግልፅ በሆኑ መመሪያዎች ማቅረብ -------------------------------------------------33
4.4.5 ቃላትን ከክሂል ትምህርቶች ጋር አቀናጅቶ ማቅረብ -----------------------------------35

ምዕራፍ አምስት፣ ማጠቃለያና አስተያት------------------------------------------------------------------ 36
5.1 ማጠቃለያ ------------------------------------------------------------------------------------------- 36
5.2 አስተያየት ------------------------------------------------------------------------------------------ 38
ዋቢ ጽሑፎች ---------------------------------------------------------------------------------------------------- 39
አባሪዎች---------------------------------------------------------------------------------------------------------- 42
አባሪ አንድ፡- ለመጽሐፉ አዘጋጆች የቀረበ ቃለ-መጠይቅ----------------------------------------------- 43
አባሪ ሁለት፡- ለመምህር 1.የተዘጋጀ ቃለ-መጠይቅ ------------------------------------------------- 44
አባሪ ሶስት: ለመምህር 2 የተዘጋጀ ቃለ- መጠይቅ----------------------------------------------------------45
አባሪ አራት: ለመምህር 3 የተዘጋጀ ቃለ- መጠይቅ----------------------------------------------------------47

## የሰንጠረዥ ማውጫ ገፅ

ሠንጠረዥ 4.1 የተተኳሪ መጽሀፉ አጠቃላይ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ---------------------------20

ሠንጠረዥ 4.2 የተተኳሪ መጽሀፉ የቃላትና የሌሎች ትምህርት ይዘቶች

ተግባራትና ጥያቄዎች ብዛት --------------------------------------------------------------------------------21

ሠንጠረዥ 4.3 በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት አደረጃጀት ---------------25

ሠንጠረዥ 4.4 የቃላት ትምህርቱ አውዳዊ አቀራረብ ------------------------------------------------26

ሠንጠረዥ 4.5 የቃላት ትምህርቱ የፍች ዝምድና አቀራረብ ---------------------------------------- 29

ሠንጠረዥ 4.6 የቃላት ትምህርት ተግባራት የመመሪያዎች አቀራረብ --------------------------- 33

ሠንጠረዥ 4.7 የቃላት ትምህርት ከክሂሎች ጋር ያላቸው ቅንጅታዊ አቀራረብ ---------------- 35

# ምዕራፍ አንድ፣ መግቢያ

ይህ ምዕራፍ የጥናትና ምርምሩ የመጀመሪያ ክፍል ሲሆን አላማውም ለጥናቱ መሰረት የሆኑ ጉዳዮችን ማሳየት ነው። በምዕራፉ መጀመሪያ የጥናቱ መሰረት ስለሆነው የቃላት ትምህርት ምንነትና ባህሪያት አስመልክቶ ንድፈ ሐሳቦች እና ጥናቶች ተዳሰዋል። ከዚያም በአነሳሽ ምክንያቱ ጥናቱን ለማካሄድ መነሻ የሆነው ሀሳብ እና ጥናቱ የመለሳቸው መሪ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ቀጥሎም የጥናቱ ዋናና ዝርዝር አላማዎች እንዲሁም ጥናቱ የሚሰጠው ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ውስንነት ነየተገለፀ ሲሆን፤ በመጨረሻም የጥናቱ ወሰን እስከምን ድረስ እንደሆነ እንዲሁም ከጥናቱ ጋር ግንኙነት ያላቸው ቁልፍ ቃላት ከዚህ ጥናት ውጭና በዚህ ጥናት ውስጥ ያላቸው ፅንሰ ሀሳባዊ ትርጓሜዎች በዝርዝር ቀርበዋል።

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ቋንቋን ለማስተማር የሚያገለግሉ መማሪያ መፃህፍት በትምህርትና በቋንቋ ሳይንስ መርሆዎች ላይ ተመስርተው በተገቢው መንገድ መዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል። በዚህ መልኩ ከተዘጋጁ የመማር ማስተማሩ ሂደት ለተማሪውም ሆነ ለመምህሩ ቀላል እንዲሆንና ፍሬያማ ውጤት እንዲያስገኝ በማድረግ በኩል ያላቸው ፋይዳ ከፍተኛ ነው።

በቋንቋ መማርያ መፃህፍት ውስጥ ከሚካተቱ ይዘቶች ውስጥ አንዱ የቃላት ትምህርት ነው። የቃላት ትምህርት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ በጣም አስፈላጊና ወሳኝ ይዘት ነው። ያለቃላት ትምህርት የተማሪዎች የቃላት እውቀት ሊዳብር አይችልም። የቃላት እውቀት ተማሪዎች ፍላጎታቸውን፣ አላማቸውን፣ ሀሳባቸውን ወዘተ. በተገቢው መንገድ ለሚመለከታቸው አካላት ለማስተላለፍም ሆነ ለመቀበል ቁልፍ ሚና አለው (Richards 2001)። Wilkins (1972) የቃላት እውቀት ያለውን አስፈላጊነት ሲያብራሩ፣ ያለሰዋስው እውቀት በተወሰነ መልኩ መግባባት ይቻላል፤ ያለ ቃላት እውቀት ግን ምንም መግባባት እንደማይቻል አስቀምጠዋል።

በአፍ መፍቻ ቋንቋ ለሚደረግ የተግባቦት ሂደት የቃላት ሚና ከፍተኛ ነው። ይሁን እንጅ ለብዙ አመታት ለቃላት ትምህርት ይሰጥ የነበረው ትኩረት ዝቅተኛ ነበር።

የቃላት ትምህርት ይዘቶች የቃላት ትምህርት ሲቀርብ ወይም ሲዘጋጅ በውስጡ ሊያካትታቸው የሚገባቸው ርዕሰ ጉዳዮች ናቸው። በቃላት ትምህርት በይዘትነት

የሚካተቱ ነጥቦችን ጠቅለል አድርገን ስናያቸው የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነሱም፡-የቃላት ፍቺ፣ የቃላት አገባብ፣ የቃላት አጠቃቀም፣ የቃላት ምስረታ እና የቃላት ንበት የሚሉት ናቸው (ማረው፣ 2003) እና (Ur፣ 2009)፡፡ የቃላት ትምህርት ይዘቶች ወሳኝ እንደ መሆናቸው መጠን በተገቢው መንገድ ለተማሪዎች ተደራሽ ሊሆኑ ይገባል፡፡ የቃላት ትምህርት ይዘቶች ለተማሪዎች ተደራሽ ሊሆኑባቸው ከሚችሉባቸው መንገዶች ውስጥ ዋነኞቹ የመማሪያ መፃህፍት ናቸው፡፡

Richards (2001) እንደገለፁት በአሁኑ ሰዓት በአለም ላይ ያሉ የቋንቋ ትምህርቶች የሚቀርቡት በመማሪያ መፃህፍት አማካኝነት ነው፡፡ መማሪያ መፃህፍት በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ የቋንቋ ትምህርት አካል ናቸው፡፡ በመርሀ ትምህርት የተነደፈው የትምህርት ይዘት ለተማሪዎች የሚደርሰው በመማሪያ መፃህፍት አማካኝነት ነው፡፡ የመማሪያ መፃህፍት በተመሳሳይ የትምህርት ደረጃ የተለያየ ቦታና ክፍል የሚገኙ ተማሪዎች ተቀራራቢ ይዘት እንዲማሩና እንዲገመገሙ በማድረግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡

መማሪያ መፃህፍት የመማር ማስተማር ሂደት አንድ አካል በመሆናቸውና አንድ የትምህርት ፕሮግራም ያለነሱ ውጤት ሊያመጣ ስለማይችል በየጊዜው ሊፈተሹና ሊገመገሙ ይገባቸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ Richards (2001) እንደጠቀሱት መማሪያ መፃህፍት የአንድን ትምህርት ይዘት በተገቢው መንገድና በተመጣጣኝ ሁኔታ ማካተታቸው መታየት አለበት፡፡ Sheldon (1988) መማሪያ መጽሀፍትን ስለ ሁለት ጉዳዮች መገምገም አስፈላጊ እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡ አንደኛው ለፕሮግራም አዘጋጆችና ለመምህራን ተገቢ መማሪያ መፃህፍትን እንዲመርጡ ሲሆን፤ ሁለተኛው መጽሀፉ አገልግሎት ላይ ከመዋሉ በፊት እና አገልግሎት ላይ እያለ ጠንካራ እና ደካማ ጎኑን ለመረዳትና ለማሻሻል ነው፡፡ በመሆኑም ተከታታይ ግምገማዎችን በማካሄድ የቋንቋ ትምህርት ደካማ ጎኖችን ማስተካከልና የትምህርት ጥራትን ማስጠበቅ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ በየጊዜው የሚታተሙ መማሪያ መፃህፍት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ሊታይና ሊገመገም ያስፈልጋል (Elley፣ 1989)፡፡

የመማሪያ መፃህፍትን ለመገምገም ምሁራን የተለያዩ መገምገሚያ መስፈርቶችን ያስቀምጣሉ፡፡ Richards (2001) እንደገለፁት በአሁኑ ግዜ የሚመረጥና የተሻለ መፃህፍት መገምገሚያ መስፈርት በDaoud and Celce -Murcian (1979) የተዘጋጀው

መስፈርት ነው፡፡ እነዚህ ምሁራን ከዘረዘሯቸው መስፈርቶች ውስጥ አንዱ ደግሞ የቃላት ትምህርት ነው፡፡ የቃላት ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መፃህፍት ዝግጅት ትኩረት ተሰጥቷቸው በጥንቃቄ ሊቀርቡ ይገባል፡፡ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽፍት ዝግጅት ወቅት የቃላት ትምህርት ይዘቶች በተገቢ ሽፋንና አቀራረብ መካተትና አለመካተታቸው ሊታይና ሊፈተሽ ይገባል፡፡ የታላሚው ቋንቋ ትምህርት ግብ እንዲመታ ቃላት በተገቢው ሁኔታ ሊመረጡና ሊቀርቡ ይገባቸዋል፡፡ በመሆኑም የተፈለገው አላማ ከግብ እንዲደርስ በመማሪያ መጽሀፍት ውስጥ የተካተቱ ቃላት ይዘቶች አደረጃጀና አቀራረብ መገምገም ያስፈረልጋል፡፡ በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙ ቃላትን ሁሉንም መማሪያ መጻህፍት ውስጥ አካቶ ማስተማር አይቻልም፡፡ በመሆኑም በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሚካተቱ የቃላት ይዘቶችን በተለያዩ መስፈርቶች መምረጥ አስፈላጊ ነው (ማረው፣ 2003)፡፡

በሀገራችን የመጀመሪያ ደረጃ መማሪያ መፃህፍት የሚዘጋጁት በክልሎች ነው፡፡ በክልሎች ከሚዘጋጁ የመጀመሪያ ደረጃ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ በደቡብ ክልል በጉራጌ ዞን አማርኛን እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ ለማስተማር የተዘጋጀው የስድስተኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ ይጠቀሳል፡፡ ይህ የመማሪያ መጽሀፍ አገልግሎት ላይ የዋለው በ2015 ዓ.ም ነው፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረትም በዚህ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቃላት ትምህርት ይዘ አደረጃጀታቸውንና አቀራረባቸውን መፈተሽ ነው፡፡ በመሆኑም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶ አደረጃጀታቸውንና አቀራረባቸውን በተመለከተ ፍተሻ ተደርጎባቸዋል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚዋ የቃላት ትምህርት ይዘቶች  አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ በደቡብ ክልል በጉራጌ ዞን በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው አዲሱ የ6ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ተተኳሪነት በሚል ርዕስ ጥናቷን እንድታካሂድ ያነሳሷት ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

የመጀመሪያው የቃላት ትምህርት ይዘት አደረጃጀትና አቀራረብን በተመለከተ በተለያየ ጊዜና ቦታ ጥናቶች ተደርገዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል ሞላ (2003) እና አልማዝ (2012) ይጠቀሳሉ፡፡

በጥናታቸውም የቃላት ትምህርቱ አደረጃጀትና አቀራረብ ችግር እንዳለበት አመልክተዋል። ከችግሮቹ መካከልም ለአብነት ያህል የቃላት ትምህርቱን ለማስተማር በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች በቂ ትኩረት አለማግኘታቸው፤ የትምህርት እርከኑን የሚመጥኑ ቃላት መረጣ በተወሰነ መስፈርቶች የተካሄደ ቢሆንም ሁሉንም አለማካተቱና በመጽሀፉ የቃላት ትምህርት ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩ፤ በምሳሌና በተብራራ መልኩ ያልቀረቡ ግልፅነት የሚጎላቸው የተወሰኑ መልመጃዎች መኖራቸው ተጠቃሽ ናቸው። ከላይ ባነሳናቸው በተለያየ ጊዜና ቦታ በቃላት ትምህርት ይዘት ላይ የተካሄዱ ጥናቶች ውስጥ የታዩ ጉድለቶች በዚህ ጥናት ተተኳሪ በተደረገው መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ መኖር ያለመኖራቸው ወይም መታየት ያለ መታየታቸው ለማረጋገጥ መታሰቡ ነው።

በሌላ በኩል መፅሀፉ አዲስ በመሆኑ ከዚህ በፊት ያልተገመገመ ስለሆነ መገምገምና መታየት የሚያሥፈልገው መሆኑ ሌላው አነሳሽ ምክንያት ነው። በመሆኑም በደቡብ ክልል በጉራጌ ዞን በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው አዲሱ  የ6ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ መፈተሽ እንዳለበት አጥኚዋ ታምናለች።

ስለሆነም፡-

1. በመማሪያ መጽሀፉ የተካተቱት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ምን ይመስላል?
2. በመማሪያ መጽሀፉ የተካተቱት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ምን ይመስላል?

የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሳት "የቃላት ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ በደቡብ ክልል በጉራጌ ዞን በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው አዲሱ  የ6ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ተተኳሪነት" በሚል ርእስ ጥናቷን አካሂዳለች።

## 1.3 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የቃላት ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ በደቡብ ክልል በጉራጌ ዞን በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው አዲሱ የ6ኛ ክፍል አማርኛ

እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ተተኳሪነት ሲሆን ይህን አጠቃላይ አላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ዝርዝር አላማዎች ተነድፈውለታል፡፡ እነሱም፡-

1. በመማሪያ መጽሀፉ የተካተቱት የቃላት ትምህርት ይዘቶችን አደረጃጀት መመርመር፤
2. በመማሪያ መጽሀፉ የተካተቱት የቃላት ትምህርት ይዘቶችን አቀራረብ መገምገም የሚሉት ናቸው፡፡

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናትና ምርምር ከዚህ በታች የተጠቀሱት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፡፡

1. ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን፡- የቃላት ትምህርቱን አቀራረብ መንገድ በመለየት የመማር ማስተማር ሂደቱን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ይረዳል፡፡
2. ለመማሪያ መጽሀፍ አዘጋጆች፡- በመጽሀፍ ዝግጅት ወቅት በቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሚካተቱ የቃላት ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ምን መምሰል እንደሚገባቸው ፍንጭ ይሰጣል፡፡
3. ለጥናት አድራጊዎች፡- በቃላት ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ዙሪያ ጥናት ለሚያደርጉ ተመራማሪዎች የመነሻ ሀሳብ እንዲሁም ማጣቀሻ በመሆን ያገለግላል ተብሎ ይታሰባል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ በደቡብ ክልል በጉራጌ ዞን በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው አዲሱ የ6ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ተተኳሪነት፡፡

በመሆኑም በመፅሀፉ የቀረቡ ሌሎች የቋንቋ ክሂሎች፣ በስነ ልሳንና በስነ ፅሁፍ ላይ ያተኮሩ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ አልተመለከተም፡፡ በሌላም በኩል በቃላት ትምህርት አሰጣጥ የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎና የመምህራን የቃላት ትምህርት አተገባበር ከዚህ ጥናት ውጭ ናቸው፡፡

## 1.6 የቁልፍ ቃላት ትርጉም

- **የቃላት ትምህርት አደረጃጀት፡-** ቃላቱን በሚመሳሰሉት ባህርይ አንፃር መቧደንና በተከታታይ ማዘጋጀትን የሚያሳይ ነው፡፡
- **የቃላት ትምህርት አቀራረብ፡-** የቃላት ትምህርት ይዘቶች መማሪያ መጽሀፍት ውስጥ የቀረቡበት መንገድ ማለት ነው፡፡

## 1.7 የጥናቱ ውስንነት

ይህ ጥናት የቃል ትምህርት ይዘት አደረጃጀት እና አቀራረብ ግምገማ በደቡብ ክልል ጉራጌ ዞን በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው አዲሱ የ ስድስተኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሃፍ ተተኳሪነት የሚል ነው፡፡ ይህ ጥናት የተካሄደው ከስራ ጎንለጎን በመሆኑም ከመደበኛው ክፍል ግዜ ውጭ ሰዓት በማመቻቸት መረጃዎችን የመሰብሰብና የመተንተን ስራው ተከናውኗል፡፡ በዚህ ጊዜ የሰዓት ማጠር ውይም የጊዜ መጣበብ እና የ መጽሀፍ አሻሻዮች በቅርብ ያለ ማግኘት እንደ ተግዳሮት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፣ ክለሳ ድርሳናት

የዚህ ምዕራፍ ዓላማ የጥናቱን ክለሳ ድርሳናት ማቅረብ ነው፡፡ በዚህ ክፍል ለጥናቱ ወሳኝ በመሆን ያገለገሉ መሰረታዊ ነጥቦች ከልዩ ልዩ መጻህፍት፣ ከታተሙና ካልታተሙ ጥናታዊ ስራዎች፣ ወዘተ. ልዩ ልዩ የመረጃ ምንጮችን ዋቢ በማድረግ ቀርበዋል፡፡ በመሆኑም እነዚህ መሰረታዊ ቁም ነገሮች የቃላት ትምህርት ምንነት ንድፈ ሐሳባዊ ቅኝት፣ የቃላት ትምህርት አቀራረብና አደረጃጀት ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት እና ከጥናቱ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ቀደምት ጥናቶች ክለሳ በሚሉ ዋና ዋና ርዕሶች ውስጥ ተካተው እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## 2.1 የቃላት ምንነት

እንግዳው (1993፣16) እንደገለጹት ቃል የትርጉም መጀመሪያ ነው፡፡ ለነገሮች፣ ለሀሳቦች፣ ለስሜቶች፣ ለፍጡሮች፣ ወዘተ. ስያሜ ወይም መጠሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ከቋንቋ መዋቅሮች ውስጥ የመግባባት መንፈስ መፀነስ የሚጀምረው በቃላት ምስረታ ላይ ነው፡፡ በሌላ በኩል ባየ (1987) ከምዕላድ ጋር በማያያዝ ቃላት አነስተኛ ወደ ሆነ ትርጉም አዘል አሀድ ሊሸነሸኑ የሚችሉ፣ ራሳቸውን ችለው የሚቆሙና በቃል ክፍል ሊመደቡ የሚችሉ የአንድ ቋንቋ ክፍሎች ናቸው በማለት ገልፀዋል፡፡

ዘሪሁን (1996፣83) እንደሚያስረዱት ከስነጽሁፍ አኳያ ቃላት ከመዝገበ ቃላት መደበኛ ፍቻቸው ውጭ እንዲሁም ከሌሎች ቃላት ጋር በመቀናጀት አውዳዊ ፍቺ ይኖራቸዋል፡፡ ይህን ተረድቶ ቃላትን በጥንቃቄ መምረጥ ያሻል፡፡ ይህን ለማድረግ የቃላትን እማሬና ፍካሬ ፍቺ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ እማሬ የቃላት መደበኛ ወይም መሠረታዊ ፍቺ ሲሆን ፍካሬ ደግሞ ከመደበኛ ፍቻቸው በተደራቢ የቋንቋው ተናጋሪዎች ወይም ደራሲው ለቃላቱ የሚሰጧቸውን ተጨማሪ ፍቺ የሚያመለክት ነው፡፡

Harmer and Rossner (1991) እንዳብራሩት ቃላት የራሳቸው የሆነ ትርጉምና አጠቃቀም እንዲሁም ቅርፅና አገባብ ያላቸው የቋንቋ ክፍሎች ናቸው፡፡ ከዚህ ጋር አያይዘው የሻው (1996) Hoket (1958)ን በመጥቀስ ቃላት በመዝገበ ቃላት ዝግጅት ከፍተኛ ስፍራ የሚሰጣቸውና የተለያዩ ፍቺዎችን ወክለው የሚገኙ የአንድ ቋንቋ አነስተኛ ክፍሎች ናቸው በማለት ገልፀዋል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ብያኔዎች መረዳት የሚቻለው ቃላት የተለያየ ትርጓሜ ያላቸው መሆኑን፤ የየትኛውም ትርጉም መጀመሪያ ቃል መሆኑን፤ ከስነ-ልሳን አንፃር ቃል የምዕላዶች ቅንጅት መሆኑንና አነስተኛ ወደ ሆነ ትርጉም አዘል አሀድ ሊከፋፈሉ የሚችሉ መሆኑን፤ ከቋንቋ መዋቅሮች ውስጥ የመግባባት ስሜት መፀነስ የሚጀምረው በቃላት ምስረታ መሆኑን፤ ከስነጽሁፍ አንፃር ሲታይ ደግሞ ቃል ከሌሎች ቃላት ጋር በመቀናጀት አውዳዊ ፍቺ እንዳላቸውና ደራሲው ቃላትን በጥንቃቄ መምረጥ እንዳለበት ያሳያል፡፡ በአጠቃላይ ቃል አውዳዊና መዝገበ ቃላዊ ፍቺ እንዳለውም ያመለክታል፡፡

## 2.2 የቃላት ትምህርት ምንነት

Ur (2009) እንደገለፁት ለቃላት ትምህርት ትኩረት መስጠት የተጀመረው በ1970ዎቹ አካባቢ ከተግባቦት ስነ-ዘዴ መምጣት ጋር ተያይዞ ነው፡፡ ምክንያቱም ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ ከቅርፅ ይልቅ ትርጉም ላለው መስተጋብራዊ ተግባር አፅንኦት ስለሚሰጥና ለዚህ ደግሞ የቃላት እውቀት አስፈላጊ በመሆኑ ነው፡፡

ወደ ቃላት ትምህርት ምንነት ስንመጣ ተማሪዎች በአንድ ቋንቋ ውስጥ ያሉ ቃላትን በተለያዩ መንገዶች ሊማሯቸው ይችላሉ፡፡ የመጀመሪያው በቋንቋ ለመዳ ሂደት በቅርበት ከሚገኙ ሰዎችና ከአካባቢው ኢ-መደበኛ በሆነ መንገድ የሚማሩበት መንገድ ሲሆን ሁለተኛው መደበኛ በሆነ መንገድ በትምህርት ቤት የሚማሩበት ሂደት ነው፡፡ መደበኛ የሆነው የቃላት ትምህርት አንድ ተማሪ በክፍል ውስጥ ከሚቀርበው የቋንቋ ትምህርት አዳዲስ ቃላትን የሚተዋወቅበት ሂደት ነው፡፡ ቃላትን ማወቅ ወይም መማር ሲባል አያሌ የቃላት እውቀት አይነቶችን ይመለከታል፡፡ ይህም የቃላቱን ቅርፅ፣ አፃፃፍ፣ ንበት፣ ፍቺ፣ ወዘተ. የሚያጠቃልል ነው Nation (2001)፡፡

## 2.3 የቃላት ትምህርት አስፈላጊነት

በቋንቋ መማር ሂደት ውስጥ የቃላት እውቀት ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ በዚህም ምክንያት በቋንቋ ትምህርት ሂደት ለቃላት ትኩረት መሰጠት እንዳለበት ምሁራን ይናገራሉ፡፡ Gains and Redman (1986) የቃላት ትምህርት በጣም አስፈላጊ እንደመሆኑ መጠን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሳይዘነጉ መካተት አለባቸው፡፡ ስለዚህ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት አዘጋጆች ቃላትን በይዘትነት በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ ማካተት እንዳለባቸው ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ ቃላትን

ማካተትን ስናስብ የትኞቹ ቃላት ከየትኞቹ በተሻለ የተማሪዎችን ክሂል ያዳብራሉ የሚለውን በመለየት እንዲሁም ካላቸው ጠቀሜታ አንፃር ተመርጠው ቢካተቱ መልካም እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

Wilkins (1972) ያለሰዋስው እውቀት በጣም ትንሽ የሆነ መልዕክት ማስተላለፍ ይቻል ይሆናል፤ ነገር ግን ያለ ቃላት እውቀት ምንም አይነት መልዕክት ማስተላለፍ አይቻልም በማለት ይገልጻሉ፡፡ ይህ የሚያመለክተን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ቃላት ከምንም በላይ አስፈላጊዎች መሆናቸውን ነው፡፡ በሌላ በኩል የቃላት እውቀት ለማንኛውም የተግባቦት ሂደት አስፈላጊ መሆኑን Nation (2001) ሲገልጹ ሰፊ የሆነ ንግግር ወይም መግለጫ የሚጀምረው ከቃላት ነው፤ ትልቅ የሚባል ድርሰትም እንዲሁ የሚነሳው ከቃል ነው ይላሉ፡፡ ስለዚህ የቃላት እውቀት አስፈላጊነት ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ጉዳይ አይደለም፡፡ የቃላት እውቀትን ስናነሳ የቃላት ትምህርት አስፈለጊነትም ተነጥሎ የሚታይ ጉዳይ አይደለም በማለት ይገልፃሉ፡፡

የቃላት ትምህርት ለሌሎች የክሂል ትምህርቶችም ሆነ የሰዋስው ትምህርት መሰረት ነው፡፡ ተማሪዎች ተገቢ በሆነ መንገድ ቃላትን ካልተማሩ ቃሉ የት ቦታ ከማን ጋር እንደሚሰለፍ ላይረዱ ይችላሉ፡፡ የቃላት ትምህርት ደግሞ የቃላትን ቅርፅና ነጠላ ፍች ከማወቅ በዘለለ የቃላት አይነቶችን እንዲለዩና ተገቢ ቃላትን በተገቢው ቦታ ላይ እንዲጠቀሙ ያስችላል (Nation፣ 2001)፡፡

የቃላት ትምህርትን አስፈላጊነት በተመለከተ Wallace (1988) በንግግር ወቅት የቃላትን ትክክለኛ ንበት (ቅላፄ) ለመጠቀም፣ የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ለመገንዘብ፣ ቃላትን ከተገቢው ቁስና ፅንሰ ሀሳብ ጋር ለማዛመድ፣ ቃላትን በተገቢው ሰዋስዋዊ ቅርፅ ለመጠቀም፣ የቃላትን ትክክለኛ ዘይቤያዊ አጠቃቀም ለመገንዘብ፣ የቃላትን የንግግር ወይም የፅህፈት ቅርፅ ለመለየትና በቃላት ተገቢውን የመደበኛነት ደረጃ ጠብቆ ለመጠቀም ያስችላል በማለት ይገልፃሉ፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ Ur (2009) እንደገለፁት የቃላት ትምህርት የሚከተሉትን ነጥቦች ለማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ እነሱም፡- የቃላትን ትክክለኛ ንበት (pronounciation) እና አፃፃፍን (spelling) ለማወቅ፣ የቃላቱን ሰዋስዋዊ መዋቅር ለመገንዘብ፣ ቃላት ከሌሎች ቃላት ጋር ያላቸውን አብሮ መጥነት (Collocation) ለመረዳትና የቃላት ፍቺ በተለያየ አውድ ለመገንዘብ የሚሉት ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ቃላት በቋንቋ ለሚከናወን ተግባቦት መሰረት ናቸው፡፡ የቋንቋ ምሁራን እንደሚገልፁትም በቋንቋ ለመዳ ሂደት ከስነ-አገባብ እውቀት በፊት በቅድሚያ የሚዳብረው የቃላት እውቀት ነው፡፡ ስለዚህም ለቋንቋ ትምህርትም መሰረቱ የቃላት ትምህርት መሆን እንዳለበት ለመረዳት አያዳግትም፡፡

## 2.4 የቃላት ትምህርት ይዘት

የቃላት ትምህርት በውስጡ የተለያዩ ይዘቶችን ያካትታል፡፡ ይህን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን እንደሚከተለው ያቀርባሉ፡፡ Nation (2001) የቃላት ትምህርት የቃላት ፍቺና የቃላት ቅርፅ ላይ የሚያተኩር መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ Ur (2009) በበኩላቸው የቃላት ትምህርት ይዘቶችን የቃላት ቅርፅ (ንበትና አጻጻፍ)፣ የቃላት ሰዋስው፣ የቃላት ክትትሎሽ፣ የቃላት አጠቃቀም (የፍቺ መስፋት)፣ የፍቺ ተዛምዶና የቃላት አመሰራረት በማለት በስድስት ከፍለው ያቀርባሉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪም Sheldon (1988) አምስት የሚሆኑ የቃላት ትምህርት ይዘቶችን ዘርዝረዋል፡፡ እነዚህም፡- የቃላት ቅርፅ፣ የቃላት ንበት፣ የቃላት አመሰራረት፣ የቃላት ፍቺና የቃላት አጠቃቀም/አገባብ ናቸው፡፡ የቃላት ትምህርት ይዘቶች በርካታ ቢሆኑም Wallace (1988) እና ማረው (2003) ጠቅለል አድርገው የቃላት አገባብ፣ የቃላት ፍቺ፣ የቃላት አጠቃቀምና የቃላት እርባታ/ምስረታ በማለት አስቀምጠዋል፡፡ የሁሉም ምሁራን ሀሳብ ተመሳሳይና እርስ በርሳቸው የሚገናኙ ስለሆኑ እንደሚከተለው ማጠቃለል ይቻላል፡ ፡ እነሱም፡- የቃላት ፍቺ፣ የቃላት አገባብ፣ የቃላት አጠቃቀም፣ የቃላት እርባታ/ ምስረታ እና የቃላት ንበት የሚሉት ናቸው፡፡

## 2.5 የቃላት ትምህርት አደረጃጀት

ቃላትን በመምረጥ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ማካተቱ ብቻ በራሱ ለቃላት ትምህርት በቂ አይሆንም፡፡ የተመረጡ ቃላት በተለያዩ መልኩ ካልተደራጁ በቀላሉ ተስተማሪ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ለቋንቋ ትምህርትነት የሚውሉ ቃላት በመምረጫ መስፈርት መመረጥ እንዳለባቸው በርካታ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም እነዚህ የተመረጡት ቃላት በምን መንገድ መደራጀት እንዳለባቸው በዝርዝር ለማየት እንሞክራለን፡፡

በቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሚቀርቡ ቃላት ተማሪዎች በቀላሉ ሊረዷቸውና ሊያስታውሷቸው በሚችሉበት ሁኔታ፣ በተወሰነ የጊዜ መጠን፣ በመደጋገምና በተለያዩ አውዶች ለመማር እድል በሚሰጥ መንገድ መደራጀት ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ Nation (2001) እንዳስቀመጡት ቃላት በቋንቋ ክንውን ውስጥ የድግግሞሽ መጠናቸውና እድገታቸውን ጠብቀው መደራጀት አለባቸው፡፡ እንዲሁም Dubin and Olshatin (1986) እንደገለፁት የቃላት አደረጃጀት በአዳዲስ ርዕሰ ጉዳይ (Topics) አቀራረብ፣ ክትትሎሽና የመጠን መመሳሰል እንዲሁም በስነ- ትምህርታዊና ስነ-ልቦናዊ መማር ማስተማር ሂደት ይመሰርታል፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ Mc Carthy (1990) ቃላትን በተለያዩ አሀዶች ከፋፍሎ በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ (Topics)፣ የቅርፅ መመሳሰልና በሚኖራቸው የፍቺ ዝምድና ማደራጀት እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡ ማረው (2003) እንዳስቀመጡት ደግሞ በመጀመሪያ ደረጃ በቃሉ ቅርጽ (አጻጻፍና ንበት) በሚመለከት፣ ቀጥሎ ቃሉ ከሌሎች ቃላት ጋር ባለው ግኑኝነትና በቃሉ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ፍቺ መሠረት አድርጎ ማደራጀት ተገቢ ነው፡፡

ምንውየለት (2005) የሽጥላ (1997፣6)ን በመጥቀስ እንደገለፁት በስነ-ልቦናዊ እሳቤዎች መሰረት ብዙውን ጊዜ ቋንቋ ከተነጣጠሉ ቅንጣቶች በጥንቃቄ በሚታቀዱ ተከታታይ ደረጃዎች ተስማሚ በሚሆኑበት ስልት ይደራጃሉ፡፡ በሌላ መንገድ የመማር ንድፈ ሀሳቦች የትምህርቱ ክትትሎሽና እድገት ከቀላል ቅርፆች ወደ ከባድ ቅርፆች፣ በተደጋጋሚ አገልግሎት ላይ ከሚውሉ አነስተኛ ድግግሞሽ ወዳላቸው፣ ተዘውታሪ ከሆኑት ተዘውታሪ ወዳልሆኑ ወዘተ. ሊደራጅ እንደሚችል ያስረዳሉ፡፡

ከላይ በተለያዩ ምሁራን የተነሱትን ቃላትን የማደራጀት መንገዶች ወደ አንድ ስናመጣቸው ቃላትን በቅርፅ ማደራጀት፣ በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ ማደራጀትና በሚኖራቸው የፍች ዝምድና ማደራጀት የሚሉትን በዝርዝር እናያለን፡፡

### 2.5.1 ቃላትን በቅርፅ ተመሳስሎ ማደራጀት

ተመሳሳይ ቅርፅ ያላቸውን ቃላት በአንድ ላይ ማቅረብ ለትምህርቱ ውጤታማነት ከፍተኛ ጥቅም አለው፡፡ እንደ Mc carthy (1990) ገለፃ ተመሳሳይ ቅጥያ የሚያስቀጥሉ ቃላት አንድ ላይ መቅረባቸውን መገንዘብ መቻል በተመሳሳይ ሁኔታ ሌሎች ቃላትን

የመመስረት ወይም የማራባት ችሎታን ያዳብራል። በመሆኑም ተመሳሳይ ቅጥያ የሚወስዱ ቃላትን በትምህርትነት አንድ ላይ አደራጅቶ ማቅረብ ተመራጭ ነው።

### 2.5.2 ቃላትን በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ ማደራጀት

በመማሪያ መፃህፍት የሚቀርቡ ቃላትን በርዕሰ ጉዳይ ማደራጀት የራሱ የሆነ ጥንካሬም ድክመትም አለው። እንደ Gairns and Redman(1986) ገለፃ በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ስር የሚጠቃለሉ ቃላትን የሚያገናኛቸውን ባህርይ በመግለፅ አደራጅቶ ማቅረብ ይቻላል። Mccarthy (1990) እንደ አብራሩት ቃላትን በርዕሰ ጉዳይ አቀናጅቶ ማቅረብ የራሱ የሆነ ችግርም አለው። ይህም ርዕሱን በትክክል ለመለየት፣ የርዕሱን ምንነት ለማወቅ፣ የትኛው ለተማሪው ጠቃሚ መሆኑን ለመለየትና የመሳሰሉትን ለማረጋገጥ አለመቻሉ የሚሉት ይጠቀሳሉ። ይሁን እንጅ ቃላትን በርዕሰ ጉዳያቸው አደራጅቶ ማቅረብ ከጉዳቱ ጥቅሙ ስለሚያመዝን ስልቱን ተጠቅሞ ማቅረብ ይቻላል።

### 2.5.3 ቃላትን በፍቺ ዝምድናቸው ማደራጀት

አንዳንድ ቃላት ሰፊ ፍቺን ወክለው ይገኛሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ጠባብ ፍቺን ይዘው የሚገኙ ቃላትም አሉ (Mccarthy፣ 1990)። ቃላትን በፍቺ ተመሳስሎ የሚደራጁበት ምክንያት ተማሪዎች ተመሳሳይ የሚመስሉ ነገር ግን በተወሰነ መጠን የሚለያዩ ቃላትን እዲለዩና ግንኙነታቸውን እንዲረዱ ለማድረግ ነው።

እንደ Gairns and Redman (1986) ገለፃ ተማሪዎች ቃሉን በሚገባ እንዲረዱ ማወቅ ያለባቸው የቃሉን ፍቺ ብቻ ሳይሆን ተዛማጂ ፍቺ ካላቸው ቃላት ጋር ያለውን ልዩነትም ጭምር ነው። ሞላ (2003) እንዳብራሩት ቃላትን በዚህ ስልት ለማደራጀት በመጀመሪያ ቃላቱ የሚገቡበትን ተገቢ አውድ መፍጠርና ቃሉን ከአውዱ ፍቺ የሚገመት ብቃትን ሊያሳድግ በሚያስችል መንገድ መቅረቡን ማረጋገጥ አለብን።

## 2.6 የቃላት ትምህርት ይዘቶች ማቅረቢያ መንገዶች

የቃላት ትምህርት በመማሪያ መፅሀፍት ውስጥ ማቅረብ የቃላቱን ዝርዝር የማቅረብ ተግባር ብቻ ሳይሆን በተማሪዎች አዕምሮ ውስጥ ስርፀው በሚቀሩበት ሁኔታ ማዘጋጀትን የሚጠይቅ ውስብስብ ሂደት ነው። በመሆኑም ለትምህርት የሚቀርቡ ቃላት የተማሪዎችን እድሜ፣ የትምህርት ዳራ፣ የትምህርቱን አላማ፣ የቃላቱን ባህርይ ያገናዘቡና ቃላቱን

በራሳቸው ለመልመድ በሚያስችሉ ስልቶች በዳበሩ መልመጃዎች ላይ የተመሰረቱ ሊሆኑ ይገባቸዋል (Gairns and Redman፣ 1986)።

የቃላት ትምህርት ቃላት እንዴት እንደሚለመዱ እና እንደሚዳብሩ በሚያሳዩ ጠንካራ እሳቤዎች ላይ በመመስረት መቅረብ አለበት በማለት ምሁራን ያስረዳሉ። ከእነዚህም ውስጥ Morgan እና Rinvolucri (1986) ቃላት አንድ ነጠላ ትርጉም ብቻ ይዘው የምናገኛቸው ብቻ ሳይሆኑ እርስ በርሳቸው የተሳሰሩ፣ በትስስሮሹ ሳቢያም የተለያዩ ቅርፆችና ፍቺዎችን የሚይዙም ናቸው። ስለዚህም ተማሪዎች አዳዲሶቹን ቃላት ከቀደመ ዕውቀታቸው ጋር እያገናዘቡ ማሰብና የመተንበይ ችሎታቸውን እየተጠቀሙ ቅርፃቸውን ከፍቺያቸው ጋር ማወቅ በሚችሉበት አኳኋን ሊቀርቡ ይገባል በማለት ያብራራሉ። እነዚሁ ምሁራን ጨምረው እንዳስረዱት የቃላት ትምህርት አቀራረብ የተነጣጠለ ሳይሆን አንደ ክንውን ቀጥሎ ካለው የተቆራኘና ደረጃ በደረጃ የተዋቀረ ሊሆን ይገባል። ይኸውም በመጀመሪያ አዳዲስ ቃላት ለተማሪዎች የሚቀርቡበት ሁኔታ ላይ ያተኩራል። በመቀጠል ተማሪዎች አዳዲሶቹን ቃላት መረዳታቸውን የሚረጋገጥበት ሂደት ይሆናል።

Ur (2009) እና Nation (2001) የሚከተሉትን የአዳዲስ ቃላት ማቅረቢያ መንገዶች ይዘረዝራሉ። እነሱም፡- እጥር ምጥን ያለ መዝገበ ቃላዊ ፍቺ፣ በጥልቀት ማብራራት፣ በተለያዩ የሰውነት እንቅስቃሴዎችና ድርጊቶች፣ ቃሉ የሚገኝበትን የተለያዩ ዕሁፎች በማቅረብ እንዲገምቱ ማድረግ፣ በተመሳሳይ ፍቺ፣ በተቃራኒ ፍቺና ተያያዥነት ያላቸውን ቃላት በማምጣት የሚሉት ናቸው።

ከላይ ከቀረቡት የምሁራን ገለጻ መረዳት እንደሚቻለው ቃላት በመማሪያ መጽሐፍት ውስጥ ሲቀርቡ የተማሪን የቀደመ እውቀት፣ ባህላዊና ማህበራዊ ዳራ፣ ወዘተ. ያገናዘቡና ተማሪዎች ቃላቱን በተለያዩ አውዶች በሚያገኟቸው ሁኔታ መሆን እንዳለባቸው የሚያስገነዝብ ነው። በቃላት የመማር ስልቶች ላይ የተካሄዱ ጥናቶች በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ ዘዴዎችን አስተዋውቀዋል። ከነዚህ የቃላት ማቅረቢያ ዘዴዎች መካከል ዋና ዋና የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው። እነሱም፡- ቃላትን በአውድ ማቅረብ፣ ቃላትን በፍቺ ዝምድናቸው ማቅረብ፣ የቃላት ትምህርትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ፣ የቃላት ትምህርቱን ግልፅ በሆኑ መመሪያዎች ማቅረብ እና ቃላትን ከቋንቋ ክሂሎች ጋር በማጣመር ማቅረብ የሚሉት ናቸው። እነዚህንም እያንዳንዳቸውን በዝርዝር እንመለከታለን።

### 2.6.1 ቃላትን በአውድ ማቅረብ

ቃላትን በአውድ ማቅረብ ቃሉ በቁሙ ከሚሰጠው ትርጉም ባሻገር በአረፍተ ነገር ውስጥ ከሌሎች ቃላት ጋር ተሰልፎ በሚያስገኘው ፍቺ መሰረት ማቅረብን የሚመለከት ነው፡፡ Lewis (1993) እንዳስቀመጡት አውድን ሁኔታዊና ስነ-ልሳናዊ አውድ በማለት በሁለት መንገድ ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ ሁኔታዊ አውድ ሲባል ቃሉን እንዳለንበት ሁኔታ መደበኛና ኢመደበኛ በሆነ አገላለፅ የምንጠቀምበት አውድ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- አንድ ሰው የቅርብ ጓደኛውን ሲያናግርና የስራ ሀላፊውን ሲያናግር የሚጠቀምባቸው ቃላት የተለያዩ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ስነ-ልሳናዊ አውድ ደግሞ ሃሳብን በመግለፅ ሂደት ቃላት ከሌሎች ቃላት ጋር የሚመጡበትና የሚነገሩበት አውድ ነው፡፡ ምሳሌ፡- በአረፍተ ነገር ውስጥ ቃላትን በአውድ ማቅረብ በተለይ ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ትክክለኛ የቃሉን አጠቃቀም እንዲረዱና ትምህርቱ አይረሴ እንዲሆን ይረዳል (Morgan and Reinvlucri፣ 1986)፡፡

ከዚህ በተጨማሪም Harmer and Rossner (1991) ተማሪዎች ቃላትን ከአውድ በመረዳት ስልት መማራቸው የሚያጋጥሟቸውን አዳዲስ ቃላት በአዕምሯቸው ለማቆየት ይረዳቸዋል በማለት የምሁራኑን ምልከታ አጠናክረዋል፡፡ Nation (2001) ቃላትን በአውድ ማቅረብ ስለሚያስገኘው ጥቅም በይበልጥ ሲያብራሩ አውድን መጠቀም ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ቃል እንዲገነዘቡ፣ ከአውድ ፍቺን እንዲያውቁ፣ ለረጂም ጊዜ ሊረሳ በማይችል ሁኔታ በአዕምሯቸው እንዲያከማቹና በአራቱ ክሂሎች ቃላትን በትክክል ለመጠቀም እንዲችሉ ተመራጭና አዎንታዊ ውጤት የሚያስገኝ የማቅረቢያ ስልት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

Morgan and Reinvlucri (1986) ተማሪዎች ቃሉን በራሳቸው እንዲማሩ ውጤታማ እንዲሆኑ ከተፈለገ ቃላትን በተገቢው አውድ አቅርቦ ማለማመድ እንደሚገባ አመልክተዋል፡፡ አንድን ቃል ከአውድ ለመረዳት አብዛኛዎቹ ቃላት የሚታወቁ መሆን አለባቸው፡፡ አለበለዚያ የቃሉን ፍቺ ከአውድ ለመገመት አስቸጋሪና ውስብስብ ይሆናል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሌላው የሚነሳው ጉዳይ የአረፍተ ነገሩ መጠን ነው፡፡ አረፍተ ነገሩ በጣም በረዘመ ወይም ባጠረ ቁጥር ለትንበያ የሚሰጡት አገልግሎት እየቀነሰ ይሄድና አስቸጋሪ ይሆናል (Nation and Coady፣ 1988)፡፡

### 2.6.2 ቃላትን በፍቺ ዝምድናቸው ማቅረብ

ተማሪዎች በከፍተኛና በመካከለኛ ደረጃ ላይ በሚሆኑበት ጊዜ ቃላትን በፍቺ ዝምድናቸው አማካኝነት ማቅረብ የቃሉን ፍቺ በቀላሉ እንዲረዱ ያደርጋል (Richards፣ 2001)። የቃላት እውቀት ሰፊ ፅንሰ ሀሳብ የያዘ እንደመሆኑ መጠን ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ቃላት በተገቢው መንገድ እንዲረዱና እንዲጠቀሙባቸው የአዳዲስ ቃላትን ፅንሰ ሀሳባዊና አገልግሎታዊ ልዩነት በሚያሳይ መንገድ ማቅረብ ተገቢ ነው። ስለዚህ ቃላትን በተመሳሳይ ፍቺ፣ በተቃራኒ ፍቺ፣ በጥቅልና በዝርዝር እንዲሁም በአብሮ መጥነት (ተሰላፊነት) ተለይተው መቅረብ አለባቸው።

#### 2.6.2.1 ቃላትን በተመሳሳይ ፍቺ ማቅረብ

ሁለት ቃላት በአንድ በተወሰነ አውድ ገብተው ተቀራራቢ ፍቺ ሲያስገኙ ሁለቱ ቃላት ተመሳሳይ ናቸው ይባላል (ምንውየለት፣ 2005)። ቃላት ፍፁም ተመሳሳይ ላይሆኑ ይችላል። በተወሰነ መጠን ደግሞ ሊለያዩ ይችላሉ። በመሆኑም በፍቺ ተመሳስሎ እንጂ በአውድ አንዱ ቃል ሌላውን ላይተካ ይችላል። ከዚህ ጋር ተያይዞ Gairns and Redman (1986) እንደገለፁት ሁለት ቃላት ፍፁም የሆነ ተመሳስሎ ቢኖራቸው ኖሮ በቋንቋው ውስጥ የሚኖራቸው ተፈላጊነት ጥያቄ ውስጥ ይገባ ነበር።

#### 2.6.2.2 ቃላትን በተቃራኒ ፍቺ ማቅረብ

አንዳንድ ቃላት በተፈጥሯቸው ወይም ከአገባባቸው በሚያስገኙት ፍቺ ተፃራሪ ሊሆኑ ይችላሉ፤ እነዚህን ቃላት ተቃራኒ ቃላት እንላቸዋለን። በቃላት መካከል መመሳሰል እንዳለ ሁሉ መቃረንም ይኖራል። በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙ ቃላት የተለያየ የተቃራኒ አይነት አላቸው። እንደ Gairns and Redman (1986) ገለፃ የሚከተሉት የተቃራኒ አይነቶች አሉ። እነሱም፡-

1. **የደረጃ ተቃርኖ፡-** የደረጃ ተቃርኖ የሚባለው እንደ ትልቅ የመሳሰለ ተቃራኒ ግንኙነት ያላቸውን ቃላት ይመለከታል። ይህ የተቃርኖ አይነት ደረጃ ሊወጣለት ይችላል። ለምሳሌ ያህልም በጣም ትልቅ፣ መካከለኛ፣ ትንሽ ወዘተ. የሚል እንደግለሰቡ ግላዊ እሳቤ ደረጃ የሚሰጣቸው መጠኖችን ያካትታል።

2. የተገላብጦሽ ተቃርኖ፡- የተገላብጦሽ ተቃርኖ የሚባለው ሁለት ቃላት በተገላብጦሽ የሚታይ ተቃራኒ ግንኙነት ያላቸው ከሆነ ነው፡፡ ምሳሌ፡- እህት/ወንድም፣ ባል/ሚስት ወዘተ. በሚሉት ቃላት መካከል ያለውን ተቃርኖ ለመግለጽ እህቱ ነች ለሚለው ወንድሟ ነው ወይም ሚስቱ ናት ለማለት ባሏ ነው ማለት ይቻላል፡፡

3. የተፃራሪ ተቃርኖ፡- ይህ ጠንከር ያለ የቃላት ተቃርኖ የሚታይበት ነው፡፡ በመሆኑም ሁለቱ ቃላት በአንድ ጊዜ በአንድ ነገር መግለጫነት ሊገቡ አይችሉም፡፡ እርስ በርሳቸው ትይዩ ናቸው፡፡ ለምሳሌ አንድ እንስሳ ወንድ ከሆነ በምንም ተዓምር ሴት ሊሆን አይችልም፡፡ በመሆኑም ወንድና ሴት፣ ጨለማና ብርሃን፣ ጧትና ማታ ጥንድ ተቃርኖ ያላቸው ናቸው፡፡

4. አቅጣጫ ጠቀስ ተቃርኖ፡- አቅጣጫ ጠቀስ ተቃርኖ የሚባለው እንደ መምጣት/ መሄድ፣ መቀመጥ/መቆም የመሳሰለ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን አቅጣጫውን የመጠቆም ባህሪ የሚታይባቸውን ተቃራኒ ቃላት የሚያጠቃልል ነው፡፡ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትንና ሌሎችንም የቃላት ፍቺ ተቃርኖዎች በጥንቃቄ በሚነደፍ መልመጃዎች አማካይነት ማቅረብና ተማሪዎቹ እንዲመረምሯቸው ማድረግ ቃላቱ ያላቸው የፍቺ ግንኙነት ገደብ እስከምን ድረስ እንደሆነ ለመረዳት እንዲችሉ ያግዟቸዋል፡፡

### 2.6.2.3 የቃላት የማጠቃለልና የመዘርዘር ሁኔታ

ከፍቺ አንፃር የቃላት ግንኙነት ከሚገለፅበት መንገድ አንዱ የቃላት አጠቃሎና ዘርዝሮ መግለፅ ነው፡፡ አንድ ቃል ሰፋ ያለ ፅንሰ ሃሳብ ይዞ የሚቀርብ ከሆነ በስሩ በርካታ የሚይዛቸው ቃላት ይኖሩታል፡፡ ለምሳሌ፡- “ጥራጥሬ” የሚለው ቃል በሱ ስር ባቄላ፣ አተር፣ ምስር፣ አደንጓሬ ወዘተ. የሚሉ ዝርዝር ቃላትን ሊይዝ ይችላል፡፡

### 2.6.2.4 የቃላት አብሮ ተሰላፊነት

በአንድ ቋንቋ ውስጥ ያሉ ቃላት እርስ በርስ ከሚያገኟቸው ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ የቃላት አብሮ መምጣት (Collocation) ነው፡፡ ይህ የቃላት ዝምድና አይነት የቃላትን አብሮ ተሰላፊነት ያሳያል፡፡ በመሆኑም ይህ ባህርይ ቃላት አብረዋቸው ከሚቀናጁ ቃላት ጋር በመሆን ቃሉ ሰፋ ያለ ፍቺ እንዲያስገኝ ያደርጋሉ፡፡ የቃላት አብሮ የመሰለፍ ሁኔታ በማንኛውም የቋንቋ ጥናት ሂደት ውስጥ ዋና የቃላት አደራጅቶ

መቅረቢያ መንገድ ነው፡፡ ይህ ባህርይ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ቃሉን እንዳይረሱና የተለያዩ የፍቺ አካባቢዎችን እንዲረዱ ያግዛል፡፡

## 2.6.3 ቃላትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ

Morgan and Reinvlucri (1986) የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ከፍ ለማድረግ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ ብለው ከዘረዘሯቸው የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ መንገዶች አንዱ ቃላትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ ነው፡፡ በሌላ በኩል Gairns and Redman (1986) እንደገለፁት በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የመዝገበ ቃላት አጠቃቀም የማይቀር የማንኛውም መርሀ ትምህርት አካል ነው፡፡ እነዚሁ ምሁራን አያይዘው እንደሚያስረዱት የአንድ ቋንቋ የቃላት ትምህርት በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ ተማሪዎች የቃሉን የተለያየ ፍቺ እንዲያውቁ ይረዳቸዋል፡፡ ተማሪዎች ከክፍል ውጭ መምህራቸውን ወይም ጓደኞቻቸውን ጠይቀው መረዳት በማይችሉበት ሁኔታ መዝገበ ቃላትን ተጠቅመው የቃሉን ፍቺ ሊረዱ ይችላሉ፡፡ ሶስት አይነት መዝገበ ቃላት እንዳሉ (Seal፣ 1991) ይገልፃሉ፡፡ የመጀመሪያው ልሳነ ክልኤ መዝገበ ቃላት ነው፡፡ ይህ መዝገበ ቃላት የታላሚውን ቋንቋ ቃላት በተማሪው አፍ መፍቻ ቋንቋ ቃላት ይተረጉማል፡፡ ሁለተኛ ልሳነ ዋህድ መዝገበ ቃላት ሲሆን የታላሚውን ቋንቋ ቃላት በዚያው በራሱ የሚፈታ መዝገበ ቃላት ነው፡፡ ሶስተኛው መደበኛ  መዝገበ ቃላት ሲሆን በአንድ ቋንቋ የሚዘጋጅና አፊ-ፊትንም ኢ-አፊ-ፊትንም ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ መዝገበ ቃላት ነው፡፡

ከላይ ከተዘረዘሩት የመዝገበ ቃላት አይነቶች ውስጥ ቋንቋውን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች በይበልጥ የተሻለ የሚሆነው ልሳነ-ክልኤ መዝገበ ቃላት ነው፡፡ ምክንያቱም ኢ-አፊፊት ተማሪዎች ቃላቱን በራሳቸው አፍ መፍቻ ተብራርተው (ተተርጉመው) ስለሚያገኟቸው በቀላሉ ያለ አጋዥ ሊረዱ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ የሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍት ሲዘጋጁ ልሳነ ክልኤ መዝገበ ቃላትን የመጠቀምንም ብልሀት ቢያካትቱ ተማሪዎች ከክፍል ውጭ ስለቃላት የሚፈልጉትን መረጃ ለማግኘት ይጠቅማቸዋል፡፡ በመሆኑም መማሪያ መፃህፍት የመዝገበ ቃላቱን የአጠቃቀም ዘዴንም ጭምር ሊያካትት ይገባል፡፡

### 2.6.4 የቃላት ትምህርትን ግልፅ በሆኑ መመሪያዎች ማቅረብ

ተማሪዎች የሚጠበቀውን የችሎታ መጠን፣ አመለካከትና የባህርይ ለውጥ እንዲያመጡ ከተፈለገ የቋንቋ መልመጃ መመሪያዎች ቋንቋ ነክ ተግባራትን የሚያካትቱና ተማሪዎችን ለልምምድ የሚጋብዙ ሆነው መቅረብ ይኖርባቸዋል (Nation፣ 2001)፡፡ በተጨማሪም Wallace (1988) እንደጠቆሙት ግልፅና በማብራሪያ የተደገፉ የቃላት ትምህርት መልመጃዎች ለማዘጋጀት በቃላት ትምህርት ዙሪያ የተሰሩ የጥናት ውጤቶችን ማየት አስፈላጊ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ተመሳሳይ ቃላትን ለማስተማር የተዘጋጁ መመሪያዎች የቃላትን የተመሳሳይነት/ልዩነት መጠንን የሚጠቁሙ ማብራሪያዎችም ቢጨመሩባቸው ተማሪዎች የቀረቡላቸውን መልመጃዎች በተፈለገው መጠን ሊሰሩ ይችላሉ፡፡

በአጠቃላይ የቃላት ትምህርት የመልመጃ መመሪያዎች በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ ሲዘጋጁ የመመሪያው ትኩረት አቅጣጫ፣ መልመጃው ያተኮረበትን ይዘትና ምሳሌዎችን በአግባቡ የያዙ መሆን አለባቸው፡፡ በተጨማሪም መመሪያዎቹ ለተማሪዎች ግልፅ፣ የተብራሩ፣ ፆታን በአግባቡ የሚገልፁና በጥንቃቄ የተቀረፁ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

### 2.6.5 ቃላትን ከክሂል ትምህርቶች ጋር በማጣመር ማቅረብ

ተማሪዎች በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን አዳዲስ ቃላት ተረድተውና አስታውሰው መጠቀም የሚችሉት የሀሳብ መቀበያ ክሂሎቻቸውን ተጠቅመው ባገኟቸው ሌሎች ቃላት አማካኝነት ነው፡፡ ቃላቱን አፍልቀው መጠቀም የሚጀምሩት በማዳመጥ ያከማቿቸውን ቃላት በመጠቀም ነው፡፡ Lewis (1993) እንደገለፁት ተማሪዎች መግባባት እንዲችሉ በተገቢው ሁኔታ በተዘጋጀ የቃላት ትምህርት መታገዝ አለባቸው፡፡ በመሆኑም የቃላት ትምህርት ከክሂል ትምህርቶች ጋር ተቀናጅተው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

## 2.7 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

የዚህ ጥናት አቅራቢ በመረጠችው ርዕስ ላይ ጥናት ለማካሄድ ከመጀመሯ በፊት ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን የቀደምት ጥናቶች ዳሰሳ አካሂዳለች፡፡ በዚህም መሰረት ከዚህ ጥናት ጋር ግንኙነት አላቸው ተብለው የታሰቡ ቀደምት ስራዎችን ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡ ጥናታዊ ስራዎቹ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረቡ ሲሆኑ ከእነዚህ

ስራዎች ውስጥ ጥቂቶቹን ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸውን ተመሳሳይነትና ልዩነት እንደሚከተለው ለመግለጽ ተሞክሯል።

ሞላ አፅብሃ (2003) “በትግራይ ክልል ለስምንተኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የቃላት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ትንተና” በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል። የጥናቱ ዋና አላማ በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን ለፈቱ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብን መገምገም ነው። በጥናቱ የተገኘው ውጤትም በመማሪያ መፅሀፉ የተወሰኑ የቃላት ትምህርት መመሪያዎች በምሳሌና በተብራራ መልኩ ተዘጋጅተው እንዳልቀረቡና ግልፅነት የሚጎላቸው እንደሆኑ፣ በብዛት ግን በተገቢው ምሳሌዎችና ማብራሪያዎች የተደገፉ መልመጃዎች እንደቀረቡ አመልክቷል።

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ከሞላ ጥናት በቃላት ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ላይ ማተኮራቸው መሳስላቸዋል። ይሁን እንጅ የሞላ ጥናት ለኢ-አፈፈት ተማሪዎች በተዘጋጀ መማሪያ መጽሀፍ ላይ ያተኮረ ሲሆን ይህ ጥናት እንደ አፍ-መፍቻ ቋንቋ በተዘጋጀመመጽሀፍ ላይ ማተኮሩ፤ በተጨማሪም በተተኳሪ መጽሀፉ እንዲሁም ጥናቱ በተካሄደበት ቦታና ጊዜ ልዩነት ስላለው ከዚህ ጥናት ጋር ይለያል።

ምንውየለት ደነቀው (2005) “በአማራ ክልል በስራ ላይ ያሉት የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍት የቃላት ትምህርት የይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ” በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል። የጥናቱ ዋና አላማ በአማራ ክልል ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን የተዘጋጁ የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፃህፍት የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ መፈተሽ ነው።

በጥናቱ የተገኘው ውጤትም በሁለቱም መማሪያ መፃህፍት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አብዛኛዎቹ በአውድ ተደግፈው መቅረባቸው፤ ቃላቱ ከቀረበላቸው አረፍተ ነገራዊ አውዶች በአብዛኛው የቃላትን ፍቺ በገቡበት ቦታ ለመገመት የሚያስችል አውዳዊ ፍንጮች ይዘው መቅረባቸው፤ ይዘት መረጣው ሁሉንም መስፈርት እንዳላሟላ፣ ይሁንና በከፊል እንዳካተተና ይህም በመፃህፍቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳሳደረ ተመላክቷል።

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ከምንውየለት ጥናት ጋር በቃላት ትምህርት ይዘት ላይ ማተኮራቸው የሚመሳሰሉበት ነጥብ ሲሆን የተተኳሪው መፅሀፍ አዲስ መሆኑና ጥናቱ በተካሄደበት ጊዜ፣ ከዚህ ጥናት ጋር በእጅጉ ይለያል።

አልማዝ ዮሀንስ (2012) "የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ የቃላት ትምህርት አደረጃጀትና አቀራረብ ፍተሻ" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል። የጥናቱ ዋና አላማም የስምንተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ የቃላት ትምህርት አቀራረብና አደረጃጀትን መመርመር ነው። በጥናቱ የተገኘው ውጤትም በመጽሀፉ ውስጥ የቃላት ትምህርቱ አቀራረብና አደረጃጀት በዋናነት ተገቢ መሆኑን፣ ይሁን እንጅ ለቃላት ፍካሬያዊ፣ ፊሊጣዊና ዘይቤያዊ ፍቺ ትኩረት እንዳላገኙ ተመላክቷል።

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ከአልማዝ ጥናት ጋር በቃላት ትምህርት ይዘት ላይ ማተኮራቸው የሚያመሳስላቸው ሲሆን የተለያዩ  መጻህፍትን ተተኳሪ ማድረጋቸው፣ የዚህ ጥናት ተተኳሪው መጽሃፍ አዲስ መሆኑ እንዲሁም ጥናቶቹ በተካሄዱበት ጊዜና ቦታ ከዚህ ጥናት ጋር ይለያል።

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡት ጥናቶች በነባሩ መማሪያ መፃህፍት ላይ የተደረጉ ሲሆን ይህ ጥናት ግን በአዲሱ ስርዓተ-ትምህርት ላይ በተዘጋጀው አዲሱ የመማሪያ መፅሀፍ ላይ የተከናወነ መሆኑ ከዚህ በፊት ከነበሩት ጥናቶች በእጅጉ ይለያል።

# ምዕራፍ ሶስት፣ የአጠናን ዘዴ

ይህ ምዕራፍ የጥናትና ምርምሩ ሶስተኛው ክፍል ሲሆን አላማውም የጥናቱን ንድፍና የአጠናን ዘዴ በግልፅ ማሳየት ነው፡፡ በውስጡም የጥቱ ንድፍ፣ የናሙና አመራረጥ ዘዴ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች እና የመረጃ አተናተን ዘዴው በዝርዝር ተብራርተው ቀርበዋል፡፡

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

ጥናቱ ይዞት ከተነሳው ጥያቄ፣ ከጥናቱ ርእስና አጠቃላይ አላማ አንጻር ገላጭ የምርምርን ንድፍ ጥቅም ላይ አውሏል፡፡ የጥናቱ አላማ የቃላት ትምህርት ይዘቶች አድረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ በደቡብ ክልል በጉራጌ ዞን በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው አዲሱ የ6ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማርያ መጽሐፍ ተተኳሪነት የሚል ነውና

ይህንን አላማ ከግብ ለማድረስ አይነታዊ ምርምር (Qualitative Research) እና መጠናዊ ምርምር (Quantitave Research) ተግባር ላይ አውሏል፡፡ ማክንያቱም መጠናዊ ምርምር በቁጥር የመረጃ ትንተና ላይ የተመሰረተ የምርምር አይነት በመሆኑ አጥኝዋ በቁጥር ለገለፀችው የመረጃ ትንተና አመቺ ሆኖ ስላገኘችው ልትመርጠው ችላለች፡፡ አይነታዊ የምርምር ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት በቃለ-መጠይቅ አማካኝነት ከመጽሀፉ አዘጋጆችና ከመምህራን በአይነት የተሰበሰቡ እና የተተነተኑ መረጃዎች በመኖራቸው ነው፡፡

## 3.2 የመረጃ ምንጮች

የዚህ ጥናት የመረጃ ምንጮች በደቡብ ክልል በጉራጌ ዞን አማርኛን እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ ለማስተማር የተዘጋጀውና በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ የዋለው አዲሱ የስድስተኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ እንዲሁም የመጽሐፉ አዘጋጆችና የ6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው፡፡

## 3.3 የናሙና አመራረጥ

### 3.3.1 የመማሪያ መጽሀፍ ናሙና አመራረጥ

የአንደኛ ደረጃ መማሪያ መጻህፍት የሚዘጋጁት በክልሎች ነው፡፡ በክልሎች ከሚዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ አማርኛን እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ ለማስተማር በደቡብ ክልል በጉራጌ ዞን በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ የዋለው የስድስተኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ ይገኝበታል፡፡ በመሆኑም ይህ የመማሪያ መፅሐፍ በዓላማ ተኮር የናሙና ዘዴ ተመርጧል፡፡ በአላማ ተኮር ዘዴ የተመረጠበት ምክንያትም የጥናቱ አቅራቢ በዚህ የክፍል ደረጃ መምህር በመሆኗና መፅሀፉ አዲስ በመሆኑ በመገምገም ያለውን ጠንካራና ደካማ ጎን መለየት አስፈላጊ መሆኑን ስላመነችበት ነው፡፡

### 3.3.2 የመምህራን እና የመጽሐፉ አዘጋጆች ናሙና አመራረጥ

አጥኚዋ በምትሰራበት ትምህርት ቤት የስድስተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ብዛት ሶስት ሲሆን ቁጥራቸው አነስተኛ በመሆኑ ሁሉም መምህራን በጠቅላይ ንሞና ዘዴ ተመርጠው በጥናቱ ተካተዋል፡፡ የመጽሐፉ አዘጋጆች ብዛት ሶስት ሲሆን ሶስቱንም ማግኘት ባለመቻሉ አንዱ አዘጋጅ ብቻ በጥናቱ ተካቶ አስፈላጊው መረጃ ተሰብስቧል፡፡

## 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ያገለገሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ሰነድ ፍተሻና ቃለ-መጠይቅ ናቸው፡፡

### 3.4.1 ሰነድ ፍተሻ

ለዚህ ጥናት በዋና መረጃ ምንጭነት አገልግሎት ላይ የዋለው የሰነድ ፍተሻ ነው፡፡ የሰነድ ፍተሻው በተተኳሪው መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የቃላት ትምህርት ይዘት አደረጃጀትና አቀራረብን ለመፈተሽ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በመሆኑም በምዕራፍ ሁለት በምሁራን የተገለፁ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ በቸክ ሊስት ከቀረቡ ዝርዝሮች አንፃር በጥናቱ ለተነሱ መሪ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጡ መረጃዎች ለመሰብሰብ አገልግሏል፡፡ በዚህም መሰረት የቃላት ትምህርት ይዘቶች በምዕራፍ ሁለት በክለሳ ድርሳኑ በምሁራን የቀረቡ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ የቃላት ትምህርት ይዘቶች ተገቢነት፣ አደረጃጀትና አቀራረባቸው ፍተሻ ተደርጎባቸዋል፡፡

### 3.4.2 ቃለ-መጠይቅ

በሰነድ ፍተሻ የተገኘውን ውጤት በአስተማማኝነት ለመደገፍ ቃለ-መጠይቅ ተዘጋጅቷል፡፡ በአጋዥ የመረጃ ምንጭነት አገልግሎት ላይ የዋለው ለአዘጋጆችና ለክፍል ደረጃው መምህራን የተዘጋጀው ቃለ መጠይቅ ነው፡፡ ቃለ-መጠይቁ በተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛን በማስተማር ሁለተኛ ዲግሪ ባላቸው ሶስት የአማርኛ መምህራን ተገምግሞ እና በአማካሪ መምህር ማሻሻያ ተደርጎበት ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡  ለአዘጋጆቹ የቀረበው ቃለ-መጠይቅ ዓላማ የመጽሐፉን የአዘገጃጀት ሂደትና በዝግጅቱ ወቅት መሰረት ያደረጓቸውን መርሆዎች ለመገንዘብ ሲሆን ለመምህራን የቀረበው ቃለ-መጠይቅ ደግሞ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቃላት ትምህርት አቀራረብና አደረጃጀትን በተመለከተ  የተመለከቱትን ጥንካሬና ክፍተት ለመረዳት ነው፡፡ በመሆኑም ከመጽሐፉ አዘጋጅና ከመምህራን አስፈላጊው መረጃ ተሰብስቦ ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ (ቃለ-መጠይቆቹን በአባሪ አንድና ሁለት ይመልከቱ) ፡፡

## 3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ከላይ በቀረቡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካኝነት መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ ወደ መረጃ መተንተኑ ስራ ተገብቷል፡፡ የመረጃ ትንተና ዘዴውም የጥናቱን መሪ ጥያቄዎች መሰረት አድርጎ ለጥያቄዎቹ ተገቢውን መልስ በሚሰጥ ሁኔታ መረጃዎቹ በአይነት በአይነት ተደራጅተው ተተንትነዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት፣ የውጤት ትንተና

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የቃላት ትምህርት ይዘቶ አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ በደቡብ ክልል በጉራጌ ዞን በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው አዲሱ የ6ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ተተኳሪነት መሆኑ በምዕራፍ አንድ ተገልጿል። በዚህ ምዕራፍ ከሰነድ ፍተሻ እና ከቃለ-መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች የጥናቱን መሪ ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ ተተንትነው ቀርበዋል። የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች በመማሪያ መጽሀፉ የተካተቱት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ምን ይመስላል? በመማሪያ መጽሀፉ የተካተቱት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ምን ይመስላል? የሚሉት ናቸው። ስለሆነም ትንተናው የጥናቱን መሪ ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ እንደሚከተለው ተደራጅቶ ቀርቧል።

## 4.1 የመጽሀፉ አጠቃላይ ዳራ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማ የተማሪዎችን የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ማጎልበት እንዲሁም የስነ-ጽሁፍና የስነ-ልሳን እውቀትን ማዳበር ነው (ትምህርት ሚኒስቴር፣ 2004)። ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ከሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች መካከል ግንባር ቀደም ተጠቃሽ የመማሪያ መጽሀፍ ነው። መማሪያ መጽሀፍ የቋንቋ ተማሪዎች የስነ ልሳንና የተግባቦት ችሎታቸውን እንዲያሻሽሉ ታስቦ የሚዘጋጅ መሆኑን (Sheldon፣1987) ገልፀዋል። የመጽሐፉ አጠቃላይ ዳራ እንደሚከተለው ቀርቧል።

በደቡብ ክልል በጉራጌ ዞን አማርኛን እንደ ደአፍ መፍቻ ቋንቋ ለሚማሩ የስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበው መማሪያ መጽሀፍ፣ የህትመት ዓመት ያልተገለፀበት ሲሆን በስራ ላይ የዋለው በ2015 ዓ.ም ነው። ይህ መጽሐፍ ምንም አንኳ የህትመት ዓመቱ ባይገለፅም ቀድሞ ስራ ላይ ከነበሩት መማሪያ መጽሀፍት ተሻሽሎ የቀረበ አዲስ መጽሀፍ ነው። የመጽሀፉ የውጭ ሽፋን ቢጫ ቀለም ያለው ሲሆን የውጭ ሽፋኑ የፊት ገፅ የፌዴራል መንግስቱ፣የክልሉ መንግስትና የክልሉን ትምህርት ቢሮ አርማ የያዘ ነው። የኋላ ሽፋኑ ላይ ደግሞ የክልሉን ትምህርት ቢሮ አርማ እና የመጽሀፉን መለያ ቁጥር (printed EMPDE 106/14 እንደሆነ ሲገለጽ የመጽሐፉ ዋጋ አልተገለጸም።

የፊት ሽፋኑ መሀል ላይ የመስማት፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ ተግባራትን የሚገልጹ ስዕላዊ መግለጫዎች ሰፍረዋል፡፡ መጽሀፉ በአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ የተዘጋጀ ሲሆን በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ትምህርት ቢሮ እና በዲላ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የክልሉን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ተስማምቶ የተዘጋጀ ነው፡፡ አስማምቶ አዘጋጆቹም አሸናፊ ደጉ፣ በቀለ ሙዳ እና ስናፍቅሽ አስፋው ናቸው፡፡

መማሪያ መጽሀፉ በአጠቃላይ በአስር ምዕራፎች የተከፋፈለ ሲሆን ሃምሳ የትምህርት ይዘቶችና 164 ገጾች አሉት፡፡ በተጨማሪም መማሪያ መጽሐፉ ከበስተጀርባው የአማርኛ የፊደል ገበታና የኢትዮጵያ ቁጥሮች ይዟል፡፡

## 4.2 በመማሪያ መጽሀፉ የቀረቡ አጠቃላይ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች መረጃ

በቋንቋ እውቀት ውስጥ የቃላት ሚና የላቀ እንደሆነና የአንድን ቋንቋ ቃላት ባንድ ጊዜና ቦታ ሁሉንም አቅርቦ ማስጠናት እንደማይቻልና ለትምህርትነት የሚቀርቡ ቃላትን መምረጥ አስፈሊጊ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ በተጨማሪም በመማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅት ሂደት ውስጥ የትኞቹ ቃላት ለተማሪዎች በመሰረታዊነት እንደሚያስፈልጉ መወሰን ዋና ጉዳይ ነው በማለት Hutchinson and Torres (1994) ይገልጻሉ፡፡

ለትምህርትነት የሚቀርቡ ቃላትን ከአስፈላጊነታቸው በመነሳት መምረጥ እንዳለብንና ልንከተላቸው የሚገቡ መስፈርቶች እንዳሉ በምእራፍ ሁለት ውስጥ ተመልክተናል፡፡ ስለዚህ በዚህ ተተኳሪ መጽሀፍ ከነዚህ የቃላት መምረጫ መስፈርቶች አንጻር እንዴት እንደተዘጋጁ ከሰነድ ፍተሻ እና ቃለ-መጠይቅ የተገኙትን መረጃዎች በማጠናቀር እንደሚከተለው ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

የመጽሀፉ አጠቃላይ ይዘት የመጽሀፉ የፊት ሽፋን የውስጥ ገጽ ላይ ተዘርዝረው ቀርበዋል፡፡ በማውጫው እንደሚታየው መጽሀፉ በአስር ምዕራፎችና በሃምሳ የትምህርት ይዘቶች የተከፋፈሉ የተለያዩ የቋንቋ ይዘቶችን አካቶ ይዟል፡፡ በመጽሀፉ የተካተቱት አጠቃላይ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርበዋል፡፡

ሰንጠረዥ 4.1 የተተኳሪ መጽሀፉ አጠቃላይ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች

| ምዕራፍ | ርዕስ | የትምህርት ይዘት |
|---|---|---|
| አንድ | ባህላዊ አለባበስ | ማዳመጥ፣ ንባብ፣ ቃላት፣ ጽህፈት፣ ሰዋስው |
| ሁለት | ታዋቂ አትሌቶች | ማዳመጥ፣ ንባብ፣ ቃላት፣ ጽህፈት፣ ሰዋስው |
| ሶስት | ቃላዊ ግጥም | ማዳመጥ፣ ንባብ፣ ቃላት፣ ጽህፈት፣ ሰዋስው |
| አራት | ዘመናዊ እርሻ | ማዳመጥ፣ ንባብ፣ ቃላት፣ ጽህፈት፣ ሰዋስው |
| አምስት | ቱሪዝም | ማዳመጥ፣ ንባብ፣ ቃላት፣ ጽህፈት፣ ሰዋስው |
| ስድስት | አደንዛዥ እጽ | ማዳመጥ፣ ንባብ፣ ቃላት፣ ጽህፈት፣ ሰዋስው |
| ሰባት | የጥላቻ ንግግር | ማዳመጥ፣ ንባብ፣ ቃላት፣ ጽህፈት፣ ሰዋስው |
| ስምንት | ኤች አይቪ ኤድስ በሽታ በኢትዮጵያ | ማዳመጥ፣ ንባብ፣ ቃላት፣ ጽህፈት፣ ሰዋስው |
| ዘጠኝ | ባህላዊ ክንዋኔዎች | ማዳመጥ፣ ንባብ፣ ቃላት፣ ጽህፈት፣ ሰዋስው |
| አስር | ሴቶችን ማብቃት | ማዳመጥ፣ ንባብ፣ ቃላት፣ ጽህፈት፣ ሰዋስው |

በሰንረዥ 4.1 ከቀረበው መረጃ እንደምንረዳው በተተኳሪ መጽሀፉ ውስጥ በእያንዳንዱ ምዕራፍ የተካተቱ ትምህርቶች ይዘቶች በማዳመጥ፣ ንባብ፣ ቃላት፣ ጽህፈት፣ ሰዋስው ላይ ያተኮሩ ናቸው። ይዘቶቹ የተደራጁት ቋንቋን በመልመድ ሂደት ቀድመው የሚመጡ ክሂሎችን በማስቀደም በትምህርት የምናዳብራቸውን ክሂሎች በማስከተል ነው። በዚህም መሰረት በክፍል አንድ ማዳመጥ፤ በክፍል ሁለት ንባብ፤ በክፍል ሶስት ቃላት፤ በክፍል አራት ጽህፈት እንዲሁም በክፍል አምስት ሰዋስው የሚሉ የትምህርት ይዘቶችቀርበዋል።

በአጠቃላይ የቀረበውን መረጃ ስንመለከት የቃላት ትምህርት በአስሩም ምዕራፍ በክፍል ሶስት ወጥ በሆነ መልኩ ራሱን የቻለ ይዘት ተደርጎ ከሌሎቹ ይዘቶች እኩል ድርሻ ተሰጥቶት ቀርቧል። ይህም ከዚህ በፊት ከነበሩት መጽሀፍት በተሻለ መልኩ ትኩረት ተሰጥቶት የተዘጋጀ መሆኑን ያመለክታል።

በመቀጠል በተከታዩ ሰንጠረዥ በመጽሀፉ ውስጥ የሚገኙ በቀጥታ የቀረቡ የቃላት ትምህርት መልመጃዎችና ተግባራት እንዲሁም በውስጣቸው የተካተቱ ጥያቄዎችን ከሌሎች የትምህርት ይዘቶች አንጻር የተሰጣቸውን ትኩረት እንመለከታለን።

**ሠንጠረዥ 4.2 የተተኳሪ መጽሀፉ የቃላትና የሌሎች ትምህርት ይዘቶች ተግባራትና ጥያቄዎች ብዛት**

| የትምህርት ይዘቶች | የመልመጃዎች ብዛት | | የጥያቄ ብዛት | |
|---|---|---|---|---|
| | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| ማዳመጥ | 42 | 19.63% | 165 | 16.98% |
| ንባብ | 50 | 23.35 | 230 | 23.66% |
| ቃላት | 31 | 14.49% | 212 | 21.81% |
| ጽህፈት | 31 | 14.49% | 85 | 8.74% |
| ሰዋስው | 30 | 14.02% | 203 | 20.89% |
| ክለሳ | 30 | 14.02% | 77 | 7.92% |
| ድምር | 214 | 100% | 972 | 100% |

በሰንረዥ 4.2 ከቀረበው መረጃ እንደምንረዳው በተተኳሪ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ መልመጃዎች ጠቅላላ ብዛት 214 ናቸው፡፡ እነዚህም 42 (19.63%) ያህሉ ማዳመጥ፣ 50 (23.35%) ያህሉ ንባብ፣ 31 (14.49%) ያህሉ ቃላት፣ 31 (14.49%) ያህሉ ጽህፈት፣ ሰዋስው 30 (14.02%) እንዲሁም 30 (14.02%) ያህሉ የክለሳ መልመጃዎች ናቸው፡፡ ከመልመጃዎቹ መካከል ከፍተኛውን የመልመጃ ብዛት የያዘው ማንበብ ሲሆን ሁለተኛውን ደረጃ የያዘው ማዳመጥ ነው፡፡ ቃላት በበኩሉ በሶስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ይህም ለቃላት ትምህርቱ ተገቢ ትኩረት የተሰጠ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል በመጽሀፉ የቀረቡ ጠቅላላ ጥያቄዎች ብዛትን ስንመለከት ማዳመጥ 165 (16.98%)፣ ንባብ 230 (23.66%)፣ ቃላት 212 (21.81%)፣ ጽህፈት 85 (8.74%)፣ ሰዋስው 203 (20.89%) እንዲሁም የክለሳ መልመጃዎች 77 (7.92%) ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት ቃላት ከንባብ 230 (23.66%) በመቀጠል 212 (21.81%) ጥያቄዎችን በመያዝ በሁለተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ማለትም በማዳመጥ፣ ንባብ እና ሰዋስው ስር 26 የቃላት ትምህርት መልመጃዎችና 195 ጥያቄዎች ይገኛሉ፡፡ ከዚህ አንጻር በቀጥታ እና በሌሎች ይዘቶች ስር ለቃላት ትምህርት የተሰጠው ትኩረት በጣም ጥሩ መሆኑን መገንዘብ እንችላለን፡፡

የቃላት ትምህርት ይዘት ተገቢነትን  በተመለከተ ለትምህርትነት የሚቀርቡ ቃላትን ከአስፈላጊነታቸው በመነሳት መምረጥ እንዳለብንና ልንከተላቸው የሚገቡ መስፈርቶች እንዳሉ በምዕራፍ ሁለት ተመልክተናል፡፡ በመሆኑም በዚህ ተተኳሪ መጽሀፍ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች ከነዚህ የቃላት ትምህርት መምረጫ መስፈርቶች አንጻር እንዴት እንደተዘጋጁ ከሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎችን እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

## 4.3 በመማሪያ መጽሀፉ የተካተቱት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ምን ይመስላል?

የቃላት ትምህርት ይዘቶች ስነ-ልሳናዊና ስነ-ትምህርታዊ መርሆችን ባገናዘበ ሁኔታ ከተመረጡ በኋላ ቀጥሎ የሚነሳው ጥያቄ ቃላቱ በመማሪያ መጽሀፍት ውስጥ እንዴት ይደራጁ? የሚለው ነው፡፡ የተመረጡ ቃላት በተለያየ መልኩ ካልተደራጁ በቀላሉ ተስተማሪ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ በምዕራፍ ሁለት በክለሳ ድርሳኑ ቃላት በቅርፅ ተመሳስሎ፣ በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ እንዲሁም በፍቺ ዝምድናቸው ተደራጅተው ሊቀርቡ እንደሚችሉ ተገልጿል፡፡ በመሆኑም በተተኳሪ መጽሀፉ የቀረቡ የቃላት ትምህርት ይዘቶች እንዴት እንደተደራጁ  ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

ሠንጠረዥ  4.3 በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት አደረጃጀት

| ተ.ቁ | የተደራጁበት ሁኔታ | የተግባራት ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በ% |
| 1 | በቅርጽ መመሳሰል | 10 | 17.54% |
| 2 | በርእሰ ጉዳይ | 22 | 38.6% |
| 3 | በፍቺ ተዛምዶ የቀረቡ | 25 | 43.86% |
| ድምር | | 57 | 100% |

በሰንረዥ 4.3 የቀረበው መረጃ የሚያሳየው በተተኳሪ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ የቃላት ትምህርት ይዘት መልመጃዎችን የአደረጃጀት ሁኔታ ነው፡፡ በዚህም መሰረት 10 (17.54%) ያህሉ በቅርፅ መመሳሰል፣ 22 (38.6%) ያህሉ በርዕሰ ጉዳይ እንዲሁም 25 (43.6%) የሚሆኑት ደግሞ በፍች ተዛምዶ የተደራጁ ናቸው፡፡ ይህም የሚያሳየን በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች የቃላት ትምህርት ይዘት

አደረጃጀትን መሰረት አድርገው የተዘጋጁ መሆናቸውን ነው፡፡ ከዚህ በመቀጠል የቃላት ትምህርት አደረጃጀትን በተመለከተ ከመማሪያ መጽሀፉ ምሳሌዎችን እንመለከታለን፡፡

**በቅርጽ መመሳሰልን መሰረት በማድረግ የተደራጁ ናሙና፡-** ምዕራፍ አስር ገጽ 154 ተግባር አራት በምሳሌው መሰረት ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ቃላት ነጻና ጥገኛ ምላዱን በመለየት በሰንጠረዥ ውስጥ ጻፉ፡፡

| ተ.ቁ | ቃላት | ነጻ ምዕላድ | ጥገኛ ምዕላድ |
|---|---|---|---|
| ምሳሌ ሀ. | ልጆቻቸውን | ልጆች | -ኦች፣ -ኣቸው፣ -ን |
| ምሳሌ ለ. | ሴትነት | ሴት | -ነት |
| 1 | ገበሬዎች | | |
| 2 | ባርኔጣዎች | | |
| 3 | ደብተሬ | | |
| 4 | ቤታቸው | | |
| 5 | ዘመዶቻቸውን | | |
| 6 | እርሳሶች | | |
| 7 | ቤተሰቦቻችሁን | | |

**ርእሰ ጉዳይን መሰረት በማድረግ የተደራጁ ናሙና፡-** ምዕራፍ ሁለት ገጽ 22 ተግባር ሶስት ቀጥሎ ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. ክለብ- ቡድን፣ ስብስብ

ለ. ማጥለቅ- ማስገባት፣ መልበስ

ሀ. ደስታ ሐ. የላቀ ሠ. አርሶአደር ሰ. እድለኛ ቀ. እርካታ

ለ. ብርታት መ. አርዓያ ረ. ዘወትር ሸ. ተቃውሞ

**የፍቺ ተዛምዶን መሰረት በማድረግ የተደራጁ ናሙና፡-** ምዕራፍ ሰባት ገጽ 105 ተግባር አንድ በ “ሀ” ስር ለቀረቡት ቃላት በ“ለ” ስር ከተዘረዘሩት በፍቺ ተመሳሳይ የሚሆኑትን እየመረጣችሁ አዛምዱ፡፡

| **ሀ** | **ለ** |
|---|---|
| 1. የውሃ ሽታ | ሀ. አንድነት |
| 2. ህብር | ለ. ግምገማ |
| 3. ቃል አቀባይ | ሐ. ብርድ |
| 4. ቆፈን | መ. ዋሾ |
| 5. ሂስ | ሠ. ደብዛው የጠፋ |
| | ረ. ወንዝ |
| | ሰ. ግለሰብ |

በአጠቃላይ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች የተደራጁት በክለሳ ድርሳኑ ምሁራን የቃላት ትምህርት ይዘት አደረጃጀት ብለው የጠቀሷቸውን የማደራጃ መስፈርቶች መሰረት በማድረግ ነው፡፡

**በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች የተደራጁት በቃላት ቅርፅ ተመሳስሎ፣ በሚያወሱት ርዕሰ ጉዳይ፣ ወይስ በፍቺ ዝምድናቸው አማካይነት ነው? ተብሎ በቃለ-መጠይቁ ቁጥር 1ለተጠየቀው ጥያቄ የመጽሀፉ አዘጋጅ የሠጡት መልስ፡፡**

በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች የተደራጁት በተዘጋጀው በመርሃ ትምህርት መሰረት ነው፡፡ በመሆኑም በመርሃ ትምህርቱ ላይ የተለያ የቃላት ትምህርት ይዘቶች ቀርበዋል፡፡ እነዚህን የቃላት ትምህርት ይዘቶች ደግሞ በአንድ መንገድ የሚቀርቡ አይደሉም፡፡ ለምሳሌ ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺዎችን እንዲሁም እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺዎችን የፍቺ ዝምድናን መሰረት በማድረግ፤ ቅጥያ ቃላትንና የቃል ክፍሎችን በቅርጽ ተማሳስሎ እንዲሁም ከምንባቡ የወጡ ቃላትን ርዕሰ ጉዳይን መሰረት በማድረግ ተደራጅተዋል፡፡ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡

**በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች የቃላት ቅርጽን፣ አንድን ርዕሰ ጉዳይ እንዲሁም የተለያዩ ፍቺዎችን መሰረት አድርገው የተደራጁ ናቸው ብለው ያስባሉ? ሀሳብዎን አብራርተው ይግለፁ፡፡ ተብለው በቃለ-መጠይቁ ቁጥር 1 ለተጠየቁት ጥያቄ ሁሉም መምህራን የሠጡት መልስ፡፡**

መምህር.1 "አዎ አስባለሁ፤ ምክንያቱም በመጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት ቃላት በእነዚህ መንገዶች የተደራጁ ናቸው። ለምሳሌ የፈሊጣዊ ቃላት፣ የእማሬያዊና ፍካሬዊ ቃላት እንዲሁም አውዳዊ ቃላትን ፍቺ ብንመለከት የተለያዩ የቃላት ፍቺን መሰረት አድርገው የተዘጋጁ ናቸው"። በማለት ሲመልሱ መምህር.2 "አብዛኛዎቹ ይዘቶች ከላይ የተዘረሩትን መስፈርቶች መሰረት አድርገው የተዘጋጁ ናቸው" በማለት መልሰዋል። መምህር.3 በበኩላቸው "አዎ አስባለሁ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች የቃላት ቅርጽን፣ አንድን ርዕሰ ጉዳይ እንዲሁም የተለያዩ ፍቺዎችን መሰረት አድርገው የተደራጁ ናቸው" የሚል መልስ ሰጥተዋል"።

በተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቃላት ትምህርትን አደረጃጀትን በተመለከተ የቃላት ቅርጽን፣ አንድን ርእሰ ጉዳይ እንዲሁም የተለያዩ ፍቾችን መሰረት አድርገው የተደራጁ እንደሆኑ፤ ለምሳሌ፡- የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊና ፈሊጣዊ አነጋገሮች በጥሩ ሁኔታ እንደተደራጁ ሁሉም መምህራን መልስ ሰጥተዋል። ከላይ ከቀረበው የመምህራን መልስ መረዳት እንደሚቻለው የተተኳሪው መጽሐፍ በሚዘጋጅበት ጊዜ የቃላት ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ትኩረት ተሰጥቶት እንደተደራጀ የሚያመላክት ነው።

በአጠቃላይ ከመጽሀፉ አዘጋጅና ከመምህራኑ የተገኙት መልሶች ከሰነድ ፍተሻ ከተገኘው መልስ ጋር ተመሳሳይ ሆኗል። በመሆኑም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች በክለሳ ድርሳኑ በምሁራን ሀሳብ የቀረቡትን የቃላት ትምህርት ይዘት ማደራጃ መስፈርቶችን ማለትም የቃላት ቅርጽን፣ አንድን ርዕሰ ጉዳይ እንዲሁም የተለያዩ ፍቺዎችን መሰረት አድርገው የተደራጁ መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል።

## 4.4 በመማሪያ መጽሀፉ የተካተቱት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ምን ይመስላል?

ለትምህርት የሚቀርቡ ቃላት በመማሪያ መጽሀፍት ውስጥ ሲቀርቡ የተማሪውን የቀደመ እውቀት፣ ባህላዊና ማህበራዊ ዳራ፣ ዕድሜ፣ የትምህርት ደረጃ በተጨማሪም የትምህርት ዓላማና ለትምህርት የቀረቡትን የአዳዲስ ቃላት ባህርይ መሰረት በማድረግ ተማሪዎች ቃላቱን በተለያዩ አውዶች በሚያገኟቸውና በሚፈልጉበት ወቅት አስታውሰው ለመጠቀም በሚያስችል መንገድ መሆን ይኖርበታል።

በክለሳ ድርሳኑ ቃላትን በአውድ ማቅረብ፣ በፍች ዝምድና ማቅረብ፣ በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ፣ ግልፅ በሆኑ መመሪያዎች ማቅረብና ከክሂል ትምህርቶች ጋር ማቅረብ የሚሉ ዋና ዋና የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ መንገዶች በምሁራን ቀርበዋል፡፡ በመሆኑም በተተኳሪ መጽሀፉ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች እነዚህን መስፈርቶች መሰረት አድርገው መቅረብ ወይም አለመቅረባቸውን እንመለከታለን፡፡

## 4.4.1 ቃላትን በአውድ ማቅረብ

ቃላትን በአውድ ማቅረብ ተማሪዎች አንድ ቃል በቁሙ ከሚሰጠው ፍቺ በተጨማሪ በተለያዩ አረፍተ ነገሮች ውስጥ ከሌሎች ቃላት ጋር በመሆን ሲገባ የተለያዩ ፍቺዎች እንደሚኖረውና የአንድን ቃል የተለያዩ ፍቺዎች እንዲገነዘቡ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡

በመሆኑም የቃላት መልመጃዎች በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ሲካተቱ ቃላቱ ከአውድ ጋር ተጣምረው የሚቀርቡና እና ተማሪዎችን ለአውድ በሚያጋልጡ መንገድ ቢቀርቡ የተሻለ መሆኑን ምሁራን ያብራራሉ፡፡ ከዚህ አንጻር በተተኳሪ መማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ የቃላት ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ምን እንደሚመስል እንመለከታለን፡፡

## ሠንጠረዥ 4.4 የቃላት ትምህርቱ አውዳዊ አቀራረብ

| ተ.ቁ | የቃላት ትምህቱ አውዳዊ አቀራረብ ሁኔታ | የተግባር ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በ% |
| 1 | በምንባብ ውስጥ ባላቸው አገባብ አንጻር | 5 | 55.56% |
| 2 | በዐረፍተ ነገር ውስጥ ባላቸው አግባብ | 2 | 22.22% |
| 3 | በዐረፍተ ነገር ውስጥ ሠርቶ ከማሳየት አንፃር | 2 | 22.22% |
| | ድምር | 9 | 100% |

በሰንረዥ 4.4 የቀረበው መረጃ የሚያሳየው በተተኳሪ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ የቃላት ትምህርት ይዘት አውዳዊ አቀራረብን ነው፡፡ በዚህም መሰረት 5 (55.56%) ያህሉ በምንባብ ውስጥ ባላቸው አገባብ አንጻር፣ 2 (22.22%) ያህሉ በተመሳሳይ በዐረፍተ ነገር ውስጥ ባላቸው አግባብና በዐረፍተ ነገር ውስጥ ሠርቶ ከማሳየት አንፃር የቀረቡ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ከቀረቡት 57 የቃላት ትምህርት ይዘቶች ውስጥ 9 (15.79% የሚሆኑት አውዳዊ አቀራረብን መሰረት አድርገው የቀረቡ ናቸው፡፡ ይህም የሚያሳየን በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አውዳዊ አቀራረብን መሰረት አድርገው በጥሩ ሁኔታ የተዘጋጁ መሆኑን ነው፡፡

እነዚህ ተግባራት በመፅሐፉ በአብዛኛው ምዕራፎች የሚገኙ ሲሆን መልመጃዎቹ በአብዛኛው ተማሪዎቹ ቃላቱን በምንባቡ ውስጥ ከገቡበት ፍቺ አንጻር ፍቺዎቻቸውን እንዲገምቱ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ይህም ተማሪዎች ብዙም ሳይቸገሩ የቃላቱን ፍቺ ከአገባብ ማወቅ እንዲችሉ ትልቅ እገዛ ያደርግላቸዋል፡፡ በተጨማሪም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት ቃላት አውድን መሠረት አድርገው መቅረባቸው ተማሪዎች የቃላት ትምህርት በሚማሩበት ጊዜ ትምህርቱ ቶሎ ስለሚገባቸው በአዕምሯቸው ውስጥ ሰርፆ እንዲቀር ከማድረግ አንፃር ጉልህ ድርሻ አለው፡፡ ከዚህ በመቀጠል የቃላት ትምህርት አውዳዊ አቀራረብን በተመለከተ ከመማሪያ መጽሀፉ ምሳሌዎችን እንመለከታለን፡፡

**በምንባብ ውስጥ ባላቸው አገባብ አንጻር ናሙና፡-** ምዕራፍ አስር ገጽ 152 ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሰረት አውዳዊ ፍቻቸውን ጽፋችሁ አሳዩ፡፡

ምሳሌ፡- ተነፍጎ ( አንቀጽ አንድ) ተከልክሎ

ደንብ ( አንቀጽ አንድ) መተዳደሪያ ህግ

ሀ. እንዲሰፍን (አንቀጽ አንድ)

ለ. ማዕቀፎች ( አንቀጽ አራት)

ሐ. ትስስር (አንቀጽ አንድ)

መ. ሚና (አንቀጽ ሁለት)

ሠ. አርዓያ (አንቀጽ ሶስት)

ረ. ማጎልበት (አንቀጽ ሶስት)

ሰ. መዋቅር (አንቀጽ አራት)

**በዐረፍተ ነገር ውስጥ ባላቸው አገባብ ናሙና፡-** ምዕራፍ ስድስት ገጽ 89 በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን አዳዲስ ቃላት በምሳሌው መሰረት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. የግል ንጽህናን አለመጠበቅ ለተስቦ በሽታ ያጋልጣል፡፡ ለተላላፊ በሽታ

ለ. ትናንት ሲያሽከረክር የነበረው ሹፌር መንገዱን ስቶ ማጥ ውስጥ ገባ፡፡

ረግረግ ቦታ (አረንቋ)

ሀ. የቁጠባ ባህል ማሳደግ የሕይወት መድህን ነው፡፡

ለ. ከግብረ-ገብነት ይልቅ ለንዋይ መሯሯጥ የስልጣኔ መገለጫ አይደለም፡፡

ሐ. የከተማው ማህበረሰብ አካባቢውን ለማጽዳት በነቂስ ወጣ፡፡

መ. የመጀመሪውን የስነ-ፅሁፍ ስራ ባለፈው ሳምንት ቋጨ፡፡

ሠ. በሀገራችን የሚስተዋሉ ህፀፆችን የማስተካከሉ ድርሻ የሁላችንም መሆን አለበት፡፡

ረ. ከትከሻዋ በታች ወርዶ የሚዘናፈለው ዞማ ፀጉሯ ውበቷን አጉልቶታል፡፡

**በአረፍተ ነገር ውስጥ ሰርቶ ከማሳየት አንጻር ናሙና፡-** ምዕራፍ ዘጠኝ ገጽ 138 የሚከተሉት ቃላት በአረፍተ ነገር ውስጥ የሚኖራቸውን አውዳዊ ፍቺ አሳዩ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ማቋረጥ | ሐ. ቅርብ | ሠ. መቋቋም |
| ለ. ከፍተኛ | መ. መቀላቀል | ረ. መጨመር |

**በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘት መልመጃዎች አውድን መሠረት አድርገው የተዘጋጁ ናቸው? ተብሎ በቃለ-መጠይቁ ቁጥር 2 ለተጠየቀው ጥያቄ የመጽሀፉ አዘጋጅ የሠጡት መልስ፡፡**

በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች ከቀረበቡበት መንገድ አንደኛው አውዳዊ አቀራረብ ነው፡፡ በመሆኑም በተለያዩ ምዕራፎች በቀረበው ምንባብ ውስጥ ባላቸው አውድ እንዲሁም በአረፍተ ነገር ውስጥ ባላቸው አውድ መሰረት የቀረቡ የቃላት ትምህርት ይዘቶች አሉ፡፡ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡

**በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘት መልመጃዎች አውድን መሠረት አድርገው የቀረቡ ናቸው ብለው ያስባሉ? ተብለው በቃለ-መጠይቁ ቁጥር 2 ለተጠየቁት ጥያቄ የተሠጠ መልስ፡፡**

መምህር.1 "አዎ አስባለሁ፤ ምክንያቱም በመጽሀፉ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች አውድን መሰረት ያደረጉ የቃላት ትምህርት ይዘቶች ቀርበዋል"፡፡ በማለት ሲመልሱ መምህር.2 "በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ከቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች ውስጥ አንዳንዶቹ አውዳዊ አቀራረብን መሰረት ያደረጉ ናቸው" በማለት መልሰዋል፡፡ መምህር.3 በበኩላቸው "አዎ አስባለሁ፤ ምክንያቱም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ በርካታ ቦታዎች ላይ አውዳዊ አቀራረብን መሰረት ያደረጉ የቃላት ትምህርት ይዘቶች ቀርበዋል" የሚል መልስ ሰጥተዋል"፡፡

ከላይ መምህራን የሰጡት መልስ ተመሳሳይነትና ተያያዥነት አላቸው፡፡ ይህም የሚያሳየው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቃላት ትምህርት በጥሩ ሁኔታ መቅረባቸውን ነው፡፡

በአጠቃላይ ከመጽሀፉ አዘጋጅና ከመምህራኑ የተገኙት መልሶች ከሰነድ ፍተሻ ከተገኘው መልስ ጋር ተቀራራቢ ናቸው፡፡ በመሆኑም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አውዳዊ አቀራረብን መሰረት አድርገው የተዘጋጁ መሆናቸውን ጥናቱ አመላክቷል፡፡

## 4.4.2 ቃላትን በፍች ዝምድና ማቅረብ

ተማሪዎች በመካከለኛና በከፍተኛ ደረጃ ላይ እያሉ ቃላትን በፍቺ ዝምድናቸው መነሻነት ማቅረብ በቀላሉ የቃሉን ፍቺ እንዲገነዘቡ እንደሚያደርግ በክለሳ ድርሳኑ ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም ለተማሪዎች አስፈላጊ የሆነውን የቃላት እውቀት ለማስጨበጥ የአዳዲስ ቃላት ፅንሰ ሀሳባዊና አገልግሎታዊ ልዩነቶችን በሚያሳይ መንገድ ማቅረብ ይገባል፡፡ በመሆኑም ቃላትን በተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቻቸው፣ የማጠቃለልና የመዘርዘር ሁኔታ እንዲሁም በቃላት በአብሮ ተሰላፊነታቸው ለይቶ ማቅረብ ተገቢ መሆኑን የዘርፉ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት በተተኳሪ መማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ይዘት መልመጃዎች ከቃላት የፍቺ ዝምዳናዎች አኳያ እንዴት እንደቀረቡ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

ሠንጠረዥ 4.5 የቃላት ትምህርቱ የፍች ዝምድና አቀራረብ

| ተ.ቁ | የቃላቱ የፍች ዝምድና አይነት | የተግባራት ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በ% |
| 1 | በፍች ተመሳስሎና ተቃርኖ የቀረቡ | 12 | 80% |
| 2 | በማጠቃለልና በመዘርዘር ሁኔታ የቀረቡ | - | - |
| 3 | በአብሮ ተሰላፊነት የቀረቡ | 3 | 20% |
| ድምር | | 15 | 100% |

በሰንረዥ 4.5 የቀረበው መረጃ የሚያሳየው በተተኳሪ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ የቃላት ትምህርት ይዘት የፍቺ ዝምድና አቀራረብን ነው፡፡ በዚህም መሰረት 12 (80%)

ያህሉ በፍች ተመሳስሎና ተቃርኖ፣ እንዲሁም 3 (20%) ያህሉ በቃላት በአብሮ ተሰላፊነት የቀረቡ ሲሆን በማጠቃለልና በመዘርዘር ሁኔታ የቀረበ የቃላት ፍቺ የለም፡፡

በሰንጠረዡ ከቀረበው መረጃ እንደምንረዳው በፍች ተመሳስሎና ተቃርኖ የቀረቡ ተግባራት ከፍተኛውን ቦታ የሚይዙ ሲሆን በቃላት አብሮ ተሰላፊነት የቀረቡ ተግባራት በበኩላቸው በጣም ዝቅተኛውን ድርሻ ይዘዋልል፡፡ የቃላት አብሮ ተሰላፊነት የአንድን ቃል ፍች አብሮት ከሚሰለፈው ቃል ፍች ጋር ለመረዳትና ሰፊ ፍችን ለማስተማር እንዲሁም በትውስታ ማህደር ለማከማቸትና የፍች አካባቢን ለመረዳት ጥቅሙ የጎላ ነው፡፡ በሌላ በኩል በማጠቃለልና መዘርዘር የቀረቡ ተግባራት በመጽሀፉ ውስጥ የሉም፡፡

በመሆኑም መጽሀፉ የቃላት አብሮ ተሰላፊነትን በጣም በዝቅተኛ ደረጃ እንዲሁም ማጠቃለልና መዘርዘርን ከነጭራሹ አለማካተቱ ትልቅ ክፍተት ነው፡፡ በአጠቃላይ የፍቺ ዝምድናን መሰረት አድርገው በመማሪያ መጽፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ተግባራት አቀራረብ ችግር ያለበት መሆኑን ከሰነድ ፍተሻ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ከዚህ በመቀጠል የቃላት ትምህርት የፍቺ ዝምድና አቀራረብን በተመለከተ ከመማሪያ መጽሀፉ ምሳሌዎችን እንመለከታለን፡፡

**በፍች ተመሳስሎና ተቃርኖ የቀረቡ ተግባራት ናሙና፡-**

***ሀ. የተመሳሳይ ፍቺ ናሙና፡-*** *ምዕራፍ ስድስት ገጽ* 87 *በ "ሀ" ምድብ ለቀረቡት ቃላትና ከ "ለ" ረድፍ በፍቺ የሚስማማውን በመምረጥ አዛምዱ፡፡*

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. መጠመድ | ሀ. መታመም |
| 2. መታወክ | ለ. ራስን አለመቻል |
| 3. ድብርት | ሐ. ምክንያት |
| 4. መንስኤ | መ. ድባቴ |
| 5. ጥገኝነት | ሠ. መያዝ |
| | ረ. እንቅልፍ |

**ለ. የተቃራኒ ፍቺ ናሙና፡-** ምዕራፍ ሶስት ገጽ 42 በ “ሀ” ረድፍ ለቀረቡት ቃላትና ሀረጋት ተቃራኒ ፍቻቸውን ከ “ለ” ረድፍ በመምረጥ በትክክል አዛምዱ፡፡

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. ቅርብ | ሀ. ከባድ |
| 2. መቀላቀል | ለ. ቀነሰ |
| 3. በሽተኛ | ሐ. ጥቂት |
| 4. ጨመረ | መ. አጸዳ |
| 5. ቀላል | ሠ. ሩቅ |
| 6. ብዙ | ረ. በርካታ |
| 7. በከለ | ሰ. መለያየት |
| 8. ጥቂት | ሸ. ጤነኛ |

**በአብሮ ተሰላፊነት የቀረቡ የቀረቡ ተግባራት መናሙና፡-** ምዕራፍ አንድ ገጽ 10 ለሚከተሉት አዳዲስ ቃላት በጽሁፍ ፍቺ ስጡ፡፡

ሀ. ቱሪስት ሐ. ሁለንተናዊ ሠ. ባህላዊ

ለ. ሀሴት መ. መገለጫ ረ. ያልተበረዘ

**በመማሪያ መጽሀፉ የቀረቡት ቃላት ቃላቱ ባላቸው የፍቺ ዝምድና አማካይነት ቀርበዋል? (ከተመሳስሎና ተቃርኖ፤ ከቃላት የማጠቃለልና የመዘርዘር ሁኔታ፤ ከቃላት አብሮ ተሰላፊነት አንጻር) ተብሎ በቃለ-መጠይቁ ቁጥር 3 ለተጠየቀው ጥያቄ የመጽሀፉ አዘጋጅ የሰጡት መልስ ፡፡**

በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች ከቀረበቡባቸው መንገዶች መካከል አንዱ የፍቺ ዝምድና ነው፡፡ ይህም ማለት ቃላቱ ባላቸው ተመሳስሎና ተቃርኖ እንዲሁም አብሮ ተሰላፊነት አንጻር መርሃ ትምህርቱን መሰረት በማድረግ እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡

**በመማሪያ መጽሀፉ የቀረቡት ቃላት ቃላቱ ባላቸው የፍቺ ዝምድና አማካይነት ቀርበዋል? ማለትም (በተመሳስሎና ተቃርኖ፤ በቃላት የማጠቃለልና የመዘርዘር ሁኔታ፤ ከቃላት አብሮ ተሰላፊነት አንጻር) ተብለው በቃለ-መጠይቁ ቁጥር 3 ለተጠየቀው ጥያቄ መምህራን የሰጡት መልስ፡፡**

*መምህር 1 "በመማሪያ መጽሀፉ የቀረቡት ቃላት በአብዛኛው በፍቺ ዝምድናቸው አማካይነት ነው፡፡ በማጠቃለልና በመዘርዘር ሁኔታ የቀረቡ ቃላት እስካሁን አላጋጠሙኝም በተመሳስሎና በተቃርኖ የቀረቡ ቃላት ግን በርካታ ናቸው"፡፡ በማለት ሲመልሱ መምህር 2 " አዎ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት ቃላት በፍቺ ዝምድናቸው የቀረቡ ናቸው" በማለት መልሰዋል፡፡ መምህር.3 በበኩላቸው "አዎ አብዛኛው ቃላት የቀረቡት በፍቺ ዝምድናቸው ነው" የሚል መልስ ሰጥተዋል"፡፡*

*ሁለቱ መምህራን "በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ቃላት ቃላቱ ባላቸው በፍች ዝምድናቸው አማካኝነት የተደራጁ ናቸው" የሚል መልስ ሲመልሱ፤ አንዱ መምህር "አብዛኛው ቦታ ላይ በፍች ዝምድናቸው አማካኝነት የቀረቡ ቢሆኑም ቃላትን በማጠቃለልና በመዘርዘር ሁኔታ የቀረበ የለም" በማለት መልሷል፡፡ እነዚህ መልሶች የሚያስረዱት በተተኳሪው መጽሐፍ ውስጥ ቃላትን በፍች ዝምድናቸው ከማቅረብ አኳያ ጥሩ ቢሆኑም ቃላትን በማጠቃለልና በመዘርዘር ሁኔታ የቀረቡ ቃላት እንደሌሉ ነው፡፡*

*በአጠቃላይ ከመጽሀፉ አዘጋጅና ከመምህራኑ የተገኙት መልሶች ከሰነድ ፍተሻ ከተገኘው መልስ ጋር ተቀራራቢ ናቸው፡፡ በመሆኑም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች ከሞላ ጎደል የቃላቱን የፍቺ ዝምድና መሰረት አድርገው የቀረቡ መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ የቃላት የማጠቃለልና የመዘሰርዘር ሁኔታ ከነጭራሹ በአንድም ቦታ አለመቅረቡ ከዚህ አንጻር ክፍተት ያለበት መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡*

## 4.4.3 ቃላትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ

*በክለሳ ድርሳኑ ምሁራን እንደገለፁት በመዝገበ ቃላት ተደግፎ የሚቀርብ የቃላት ትምህርት አቀራረብ በአጠቃቀም ብልሃት ላይ ትኩረት አድርጎ ከቀረበ ተማሪዎች ከክፍል ውጭ ባስፈለጋቸው ጊዜ ስለቃላት የሚፈልጉትን መረጃ ለማግኘት መዝገበ ቃላትን*

የመጠቀም ልምድ እንዲያዳብሩ ከማድረግ አንፃር ድርሻው የጎላ ነው። በመሆኑም በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ በመዝገበ ቃላት ተደግፎ የሚቀርብ የቃላት ትምህርት ተግባር ስለ አጠቃቀም አንዳንድ መመሪያ በመስጠት ጭምር ሊቀርብ ይገባል።

በዚህም መሰረት በተተኳሪ መጽሀፉ ውስጥ መዝገበ ቃላትን ተደግፈው የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች በአዛምድ መልክ እና ቀጥታ በመዝገበ ቃላት በመታገዝ ፍቻቸውን እንዲፈለጉ የሚያዙ ናቸው። ይሁን እንጂ በምን መንገድ እንደሚፈልጉ የሚገልፅ ወይም የሚጠቁም ነገር የለውም። በሌላ በኩል መዝገበ ቃላትን አስደግፎ ማቅረብን የተመለከቱ ተግባራት በብዛት መቅረብ ሲኖርባቸው በመጽሀፉ የቀረቡ ተግባራት ሁለት ብቻ ናቸው። ይህም በተማሪዎቹ የቃላት እውቀት ላይ የራሱ የሆነ ተፅእኖ ማሳደሩ የማይቀር ነው። ምክንያቱም ተማሪዎች በቂ የመዝገበ ቃላዊ ፍች ትምህርት ካላገኙ ይአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ስላልሆነ የቃላትን መዝገበ ቃላዊ ፍች የማወቅ ውስንነት ይኖርባቸዋል። መዝገበ ቃላትንም መጠቀም ያስፈልጋቸዋል። ስለዚህ የመማርያ መጽሐፉን እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ ያውቁ ዘንድ በመማርያ መጽሐፉ ውስጥ በመዝገበ ቃላት ትምህርት በአብዛኛው ቦታ መቅረብ ነበረባቸው።

በአጠቃላይ በመማሪያ መጽሀፉ በመዝገበ ቃል በመደገፍ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች በቁጥር አነስተኛ ከመሆናቸውም በላይ በግልጽ መመሪያ አለመቅረባቸው በድክመትነት የሚታይ ነው።

**በመዝገበ ቃል ተደግፈው የቀረቡ ተግባራት ናሙና፡-** ምዕራፍ ሰባት ገጽ 104 የሚከተሉትን ቃላት ከመዝገበ ቃላት ፍቻቸውን ፈልጋችሁ በደብተራችሁ ጻፉ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. አብነት | መ. ለበጣ | ሰ. ዳጎሰ | በ. ብርሃን |
| ለ. ደባ | ሠ. ሙስና | ሸ. አጤነ | |
| ሐ. ምናብ | ረ. ሰርግና ምላሽ | ቀ. አጥቢያ | |

**በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች በመዝገበ ቃላት ተደግፈው ቀርበዋል? ተብሎ በቃለ-መጠይቁ ቁጥር 4 ለተጠየቀው ጥያቄ የመጽሀፉ አዘጋጅ የሰጡት መልስ ፡፡**

በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች ከቀረቡባቸው መንገዶች መካከል አንዱ የቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ነው። ምንም እንኳን በቂ ባይሆኑም

በመጽሀፉ ውስጥ አንዳንድ ቦታ ላይ ተማሪዎቹ መዝገበ ቃላትን ተጠቅመው የቃላቱን ፍቺ እንዲገልጹ የሚያደርጉ መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡

**በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች በመዝገበ ቃላት ተደግፈው ቀርበዋል ብለው ያስባሉ? ተብለው በቃለ-መጠይቁ ቁጥር 4 ለተጠየቀው ጥያቄ መምህራን የሰጡት መልስ ፡፡**

ሁሉም መምህራን በተመሳሳይ መልኩ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ በመዝገበ ቃላት የተደገፉ የቃላት ትምህርት ይዘቶች መኖራቸውንና ቁጥራቸው አነስተኛ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ መምህራን ከሰጡት መልስ መገንዘብ እንደሚቻለው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በመዝገበ ቃላት ተደግፈው የቀረቡት የቃለት ትምህርት ይዘቶች ውስን መሆናቸውን ነው፡፡

በአጠቃላይ ከመጽሀፉ አዘጋጅና ከመምህራኑ የተገኙት መልሶች ከሰነድ ፍተሻ ከተገኘው መልስ ጋር የተጣጣሙ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በመማሪያ መጽሀፉ በመዝገበ ቃል በመደገፍ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች በቁጥር አነስተኛ ከመሆናቸውም በላይ በግልጽ መመሪያ አለመቅረባቸው በድክመትነት የሚታይ ነው፡፡ በመሆኑም ቃላትን በመዝገበ ቃል አስደግፎ ከማቅረብ አንጻር ክፍተት ያለበት መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡

## 4.4.4 ቃላትን ግልፅ በሆኑ መመሪያዎች ማቅረብ

የቃላት ትምህርት መልመጃዎች ለተማሪዎች ሲቀርቡ ለመለማመድ እንዲያግዛቸው ግልፅ ሆኖ በተብራራ ሁኔታ የሰፈረ መመሪያ ሊኖረው እንደሚገባ በክለሳ ድርሳኑ ተብራርቷል፡፡ ይህም የሚያመለክተን የቃላት ትምህርት ተግባራትና መልመጃዎች የቀረቡበት ዓላማ ከግብ የሚደርሰው መመሪያዎቹ ለተማሪዎች ግልፅ ሆነው ሲቀርቡ መሆኑን ነው፡፡ ተማሪዎች የቀረቡላቸው መልመጃዎች ገብቷቸው ሊለማመዱ የሚችሉት በመጽሀፉ የሚቀርቡ ተግባራት በግልጽ መመሪያዎችና ምሳሌዎች ተደግፈው ሲቀርቡ ነው፡፡ ይህንንም መሰረት በማድረግ በተተኳሪ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ የቃላት ትምህርት ተግባራት በግልጽ መመሪያዎች የተደገፉ መሆን አለመሆናቸውን በሰነድ ፍተሻታይቷል፡፡

ሠንጠረዥ 4.6 የቃላት ትምህርት ተግባራት የመመሪያዎች አቀራረብ

| ተ.ቁ | የመመሪያዎች አቀራረብ ሁኔታ | የተግባር ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በ% |
| 1 | በምሳሌ የተደገፉ | 15 | 26.32% |
| 2 | በምሳሌ ያልተደገፉ | 42 | 73.68% |
| ድምር | | 57 | 100% |

በሰንረዥ 4.6 የቀረበው መረጃ የሚያሳየው በተተኳሪ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ የቃላት ትምህርት ተግባራት የመመሪዎች አቀራረብን ነው፡፡ በዚህም መሰረት 15 (26.32%) ያህሉ በምሳሌ የተደገፉ ሲሆን 42 (73.68%) የሚሆኑት በምሳሌ ያልተደገፉ ናቸው፡፡ ይህ የሚያመለክተው በመጽሀፉ ለመመሪያ አቀራረብ ትኩረት እንዳልተሰጠው ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በአብዛኛዎቹ የግልፅነት ችግር ይታይባቸዋል፡፡ ተገቢውን ስርዓት ነጥብ ያለመሟላትና ምን እነደሚያዙ ግልፅ ያለመሆን ችግር ይስተዋላል፡፡

**በምሳሌ ተደግፈው የቀረቡ ተግባራት መናሙና፡-** ምዕራፍ ስድስት ገጽ 89 በሚከተሉት ቃላት በምሳሌው መሰረት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ስጡ፡፡

**ምሳሌ፡-** ጉቶ፡- እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺው የእንጨት ተቆርጦ ከስር የሚቀረው አካል ሲሆን ፍካሬያዊ ፍቺው አጭር

ሀ. እስስት　　መ. ቁልፍ　　ሰ. ማር

ለ. ምሰሶ　　ሠ. አልጋ　　ሸ. ተልባ

ሐ. ቋንጣ　　ረ. ኩራዝ

**በምሳሌ ተደግፈው ያልቀረቡ ተግባራት መናሙና፡-** ምዕራፍ አንድ ገጽ 11 ቀጥሎ የተዘረዘሩት ቃላት በምንባቡ ውስጥ ባላቸው አውዳዊ ፍቺ መሰረት አረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡

ሀ. ያሸበረቀ　　ሐ. አሻራ　　ሠ. ጥበብ

ለ. ፈጠራ　　መ. አዛውንት

**በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘት ተግባራት በግልጽ መመሪያዎችና ምሳሌዎች የቀረቡ ናቸው ? ተብሎ በቃለ-መጠይቁ ቁጥር 5 ለተጠየቀው ጥያቄ የመጽሀፉ አዘጋጁ የሰጡት መልስ ፡፡**

በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ተግባራት በግልጽ መመሪያዎች የቀረቡ ናቸው፡፡ ይህም ማለት ተማሪዎቹ ምን ተግባር መስራት እንዳለባቸው በግልጽ በሚያብራራ መልኩ የቀረቡ ናቸው፡፡ ምሳሌን በተመለከተ ለተማሪዎቹ ሊከብዱ ይችላል ተብለው የታሰቡ ተግባራት ላይ እንዴት መስራት እንዳለባቸው ምሳሌዎች ቀርበዋል፡፡ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡

**በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘት ተግባራት በግልጽ መመሪያዎችና ምሳሌዎች የቀረቡ ናቸው ብለው ያስባሉ? ተብለው በቃለ-መጠይቁ ቁጥር 5 ለተጠየቀው ጥያቄ መምህራን የሰጡት መልስ ፡፡**

መምህር1 "በመማሪያ መጽሀፉ የቀረቡት አብዛኛዎቹ የቃላት ትምህርት ይዘት ተግባራት በግልጽ መመሪያዎች የቀረቡ ናቸው፡፡ ምሳሌን በተመለከተ አንዳንድ ቦታ ላይ ብቻ ነው የተሰጠው"፡፡ በማለት ሲመልሱ መምህር.2 እና መምህር 3 በተመሳሳይ መልኩ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘት ተግባራት በግልጽ መመሪያዎች የቀረቡ መሆናቸውንና በቂ ምሳሌዎች ያልተሰጡ መሆናቸውን አብራርተዋል፡፡

ከላይ የተሰጡት የመምህራን ምላሾች የሁሉም ተመሳሳይ ሲሆኑ ይህም በመምሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘት ተግባራት አብዛኛው ቦታ ላይ በግልጽ መመሪያዎች እንደቀረቡና በምሳሌ አስደግፌው ከማቅረብ አንጻር ግን ክፍተት እንደለባቸው ገልጸዋል፡፡

በአጠቃላይ ከመምህራኑ የተገኙት መልሶች ከሰነድ ፍተሻ ከተገኘው መልስ ጋር ከሞላ ጎደል ተቀራራቢ ናቸው፡፡ ከመጽሀፉ አዘጋጅ የተገኘው መልስ ከሰነድ ፍተሻው ከተገኘው መረጃ ጋር ተቃራኒ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዋናው የሰነድ ፍተሻ የተገኘው መረጃ መጽሀፉ የቃላት ትምህርት ይዘት ተግባራትን በግልጽ መመሪያዎችና ምሳሌዎች የማቅረብ ክፍተት ያለበት መሆኑን ያመለክታል፡፡

### 4.4.5 ቃላትን ከክሂል ትምህርቶች ጋር አቀናጅቶ ማቅረብ

ተማሪዎች ቃላቱን በሚገባ እንዲረዷቸውና አይረሴ በሆነ መንገድ እንዲገነዘቧቸው ከክሂል ትምህርቶች ጋር ሊለማመዷቸው ይገባል፡፡ ተማሪዎች ያገኟቸውን አዳዲስ ቃላትን አስታውሰው ትርጉም ባለው አውድ መጠቀም የሚችሉት የመቀበያ ክህሎችን ተጠቅመው ባገኙት እውቀት ነው፡፡ በመሆኑም የቃላት ትምህርቱን ከክሂሎች ጋር በማቀናጀት ማቅረብ ትምህርቱን ከክሂሎች የተቃና ያደርገዋል፡፡ ከዚህ አንፃር በተተኳሪ መጽሐፍት ውስጥ የቀረቡ ትምህርቶችን በሠንጠረዥ እንመለከት፡፡

**ሠንጠረዥ 4.7 የቃላት ትምህርት ከክሂሎች ጋር ያላቸው ቅንጅታዊ አቀራረብ**

| ተ.ቁ | የተግባራቱ የአቀራረብ ሁኔታ | የተግባር ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በ % |
| 1 | ከክሂል ትምህርት ጋር በቅንጅት የቀረቡ | 26 | 45.61% |
| 2 | ራሳቸውን ችለው ለብቻቸው የቀረቡ | 31 | 54.39% |
| ድምር | | 57 | 100% |

በሰንረዥ 4.7 የቀረበው መረጃ የሚያሳየው በተተኳሪ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ የቃላት ትምህርት ይዘቶች ከሌሎች የክሂል ትምህት ይዘቶች ጋር ያላቸውን ቅንጅታዊ አቀራረብ ነው፡፡ በዚህም መሰረት መጽሀፉ ውስጥ ከቀረቡ 57 ተግባራት ውስጥ 26 (45.61%) ያህሉ ከክሂል ትምህርት ጋር ማለትም ከማዳመጥ፣ ከንባብ፣ ከሰዋሰው ትምህርት ጋር ተቀናጅተው የቀረቡ ሲሆን የቀሩት 31 (54.39%) የሚሆኑት ተግባራት ራሳቸውን ችለው የቀረቡ ናቸው፡፡ ይህ የሚያመለክተው በመጽሀፉ ለክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ የተሻለ ትኩረት የሰጠ መሆኑን ነው፡፡

**ከክሂል ትምህርት ጋር በቅንጅት የቀረቡ የቃላት ትምህርት ይዘቶች ናሙና፡-** ምዕራፍ አንድ ገጽ 6 በአዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ለሚከተሉት ቃላት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡

ሀ. ትውፊት ሐ. ሽማ ሰሪ ሠ. አጥቢያ

ለ. ሀገርኛ መ. በየፈርጁ

**በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት ቃላት ይዘት መልመጃዎች ከሁሉም የቋንቋ ክሂሎች ጋር ግንኙነት ፈጥረው የተዘጋጁ ናቸው? ተብሎ በቃለ-መጠይቁ ቁጥር 6 ለተጠየቀው ጥያቄ የመጽሀፉ አዘጋጅ የሰጡት መልስ፡፡**

በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ተግባራት ራሳቸውን ችለው ቃላት በሚል ርዕስ ስር ከመቅረባቸው በተጨማሪ ከማዳመጥ፣ ከንባብና ከሰዋስው ይዘቶች ጋር በቅንጅት የቀረቡ ተግባራት በርካታ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ከንባብ በኋላ ከንባቡ ለወጡ ቃላት አውዳዊ ፍች ስጡ የሚሉ ተግባራቶች አሉ፡፡ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡

**በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ይዘት መልመጃዎች ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር ያላቸው ግንኙነት ምን ይመስላል? ተብለው በቃለ-መጠይቁ ቁጥር 6 ለተጠየቁት ጥያቄ መምህራን የሰጡት መልስ፡፡**

ሁሉም መምህራን ተመሳሳይ በሆነ መልኩ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ይዘት መልመጃዎች ራሳቸውን ችለው ከመቅረባቸው ባሻገር ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅተው በተለያ ቦታዎች ላይ የቀረቡ መሆናቸውን አብራርተዋል፡፡ መምህራኑ ከሰጡት መልስ የምንረደው በመሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቃላት ትምህርት ይዘት መረጃዎች ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር በጥሩ ሁኖታ ተቀናጅተው የቀረቡ መሆናቸውን ነው፡፡

በአጠቃላይ ከመጽሀፉ አዘጋጅና ከመምህራኑ የተገኙት መልሶች ከሰነድ ፍተሻ ከተገኘው መልስ ጋር የተጣጣመ ነው፡፡ በመማሪያ መጽሀፉ ከቀረቡት 57 የቃላት ትምህርት መልመጃዎች መካከል 26 የሚሆኑት ከሌሎች ክሂሎች ጋር በቅንጅት የቀረቡ መሆናቸውን በሰነድ ፍተሻው ታይቷል፡፡ ይህ የሚያመለክተው በመጽሀፉ የቀረቡት የቃላት ይዘት ተግባራት ራሳቸውን ችለው ከመቅረባቸውም ባሻገር ከሌሎች ክሂሎች ጋር በቅንጅት የቀረቡ መሆናቸውን ነው፡፡

# ምዕራፍ አምስት፣ ማጠቃለያና አስተያት

የዚህ ምዕራፍ ዋና ዓላማ የጥናቱን ማጠቃለያና አስተያየት መግለፅ ነው። ስለሆነም የጥናቱን ውጤት መሰረት በማድረግ ማጠቃለያና አስተያየቶች በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የቃላት ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ በደቡብ ክልል በጉራጌ ዞን በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው አዲሱ የ6ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ተተኳሪነት ነበር። ይህንን አጠቃላይ አላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሁለት ዝርዝር አላማዎች ተነድፈውለታል። እነሱም፡- በመማሪያ መጽሀፉ የተካተቱት የቃላት ትምህርት ይዘቶችን አደረጃጀት መመርመር እና በመማሪያ መጽሀፉ የተካተቱት የቃላት ትምህርት ይዘቶችን አቀራረብ መገምገም የሚሉት ናቸው።

እነዚህን ዝርዝር አላማዎች ለማሳካትና በጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ስር የቀረቡትን መሪ ጥያቄዎች ለመመለስ በ2015 ዓ.ም በክልል አቀፍ ደረጃ አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር የተዘጋጀውን የ6ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ በሰነድ ፍተሻ በመመርመር እንዲሁም የመጽሀፉን አዘጋጅና መምህራንን ቃለ-መጠይቅ በማድረግ የተገኙት መረጃዎች ተሰብስበው ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል። የትንተናውን ውጤት መሰረት በማድረግም የሚከተለው ማጠቃለያ ላይ ተደርሷል።

ከጥናቱ ዝርዝር አላማዎች የመጀመሪያው የጥናቱ አላማ በመማሪያ መጽሀፉ የተካተቱት የቃላት ትምህርት ይዘቶችን አደረጃጀት መመርመር የሚለው ነው። ይህንን አላማ ለማሳካት ጥናቱ በምሁራን የተገለጹ ሶስት የቃላት ትምህርት ይዘት ማደራጃ መስፈርቶችን ጥቅም ላይ አውሏል። እነዚህ መስፈርቶችም ቃላትን በቅርፅ ተመሳስሎ፣ በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ እንዲሁም በፍቺ ዝምድናቸው ማደራጀት የሚሉ ናቸው። በመሆኑም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች የቃላት ትምህርት ይዘት አደረጃጀት መስፈርትን ማለትም የቃላት ቅርጽን፣ አንድን ርዕሰ ጉዳይ እንዲሁም የተለያዩ ፍቺዎችን መሰረት አድርገው በጥሩ ሁኔታ የተደራጁ መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል።

የመጨረሻው የጥናቱ ዓላማ በመማሪያ መጽሀፉ የተካተቱት የቃላት ትምህርት ይዘቶችን አቀራረብ መገምገም የሚለው ነው፡፡ ይህንን ዓላማ ለማሳካት ጥናቱ በምሁራን የተገለጹ አምስት የቃላት ትምህርት ይዘት ማቅረቢያ መስፈርቶችን ጥቅም ላይ አውሏል፡፡ እነዚህ መስፈርቶችም ቃላትን በአውድ ማቅረብ፣ በፍች ዝምድና ማቅረብ፣ በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ፣ ግልፅ በሆኑ መመሪያዎች ማቅረብና ከክሂል ትምህርቶች ጋር ማቅረብ የሚሉ ናቸው፡፡

እነዚህን መስፈርቶች መሰረት አድርገን ስንመለከት ቃላትን በአውድ ከማቅረብ አንጻር በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አውዳዊ አቀራረብን መሰረት አድርገው በጥሩ ሁኔታ የተዘጋጁ መሆኑን፤ በፍች ዝምድና ከማቅረብ አንጻር በመማሪያ መጽሓፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ተግባራት አቀራረብ ችግር ያለበት መሆኑን፤ በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ከማቅረብ አኳያ በመማሪያ መጽሀፉ በመዝገበ ቃል በመደገፍ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች በቁጥር አነስተኛ ከመሆናቸውም በላይ በግልጽ መመሪያ አለመቅረባቸው ትልቅ ክፍተት መሆኑን፤ ግልፅ በሆኑ መመሪያዎች ከማቅረብ አኳያ መጽሀፉ የቃላት ትምህርት ይዘት ተግባራትን በግልጽ መመሪያዎችና ምሳሌዎች የማቅረብ ክፍተት ያለበት መሆኑን፤ ከክሂል ትምህርቶች ጋር አቀናጅቶ ከማቅረብ አንጻር መጽሀፉ ለክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ የተሻለ ትኩረት የሰጠ መሆኑን፤ በአጠቃላይ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች በአብዛኛው በምሁራን የተገለጹትን የቃላት ትምህርት አቀራረብ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ የቀረቡ መሆናቸውን የመረጃ ትንተናው ውጤት ያመለክታል፡፡

## 5.2 አስተያየት

ከላይ በማጠቃለያው እንደተገለጸው በጥናቱ የተነሱትን ጥያቄዎችና አላማዎች መነሻ በማድረግ በተተኳሪ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡትን የቃላት ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ በምሁራን የቀረቡ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ ግምገማ ተካሂዷል፡፡ በጥናቱ ውጤት መሰረትም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት አደረጃጀት በጥሩ ሁኔታ የተደራጀ መሆኑ፤ የቃላት ትምህርት አቀራረብን በተመለከተ በፍች ዝምድና ከማቅረብ አንጻር በመማሪያ መጽሓፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ተግባራት አቀራረብ ችግር ያለበት መሆኑ፤ በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ከማቅረብ አኳያ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ በመዝገበ ቃል በመደገፍ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች

በቁጥር አነስተኛ ከመሆናቸውም በላይ  በግልጽ መመሪያ አለመቅረባቸው ትልቅ ክፍተት መሆኑ፤ ግልፅ በሆኑ መመሪያዎች ከማቅረብ አኳያ መጽሀፉ  የቃላት ትምህርት ይዘት ተግባራትን በግልጽ መመሪያዎችና ምሳሌዎች የማቅረብ ክፍተት ያለበት መሆኑ በድክመት ተነስቷል። በመሆኑም አጥኚዋ የጥናቱን ውጤት መሰረት በማድረግ ከዚህ በታች የቀረቡትን በአስተያየቶች አቅርባለች።

- **ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን፡-** በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ በመዝገበ ቃል በመደገፍ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች በቁጥር አነስተኛ ከመሆናቸውም በላይ በግልጽ መመሪያ አለመቅረባቸው ትልቅ ክፍተት መሆኑ በተጨማሪም መጽሀፉ የቃላት ትምህርት ይዘት ተግባራትን በግልጽ መመሪያዎችና ምሳሌዎች የማቅረብ ክፍተት ያለበት መሆኑ በድክመት ተነስቷል። በመሆኑም መምህራን በመዝገበ ቃላት በመደገፍ ተማሪዎቻቸውን ቃላት ቢያስተምሩ እንዲሁም በግልጽ መመሪያዎችና ምሳሌዎች ያልቀረቡ ተግባራትን ግልጽ መመሪያና ምሳሌ በመስጠት ተማሪዎቹ እንዲሰሩ ቢያደርጉ የተማሪዎችን የተለያዩ የቃላት እውቀት ለማዳበር ይረዳቸዋል።
- **ለመማሪያ መጽሀፍ እና ለመርሐ ትምህርት አዘጋጆች፡-** በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ተግባራት አቀራረብ ችግር ያለበት መሆኑ፤ በመዝገበ ቃል በመደገፍ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች በቁጥር አነስተኛ ከመሆናቸውም በላይ  በግልጽ መመሪያ አለመቅረባቸው ትልቅ ክፍተት መሆኑ፤ የቃላት ትምህርት ይዘት ተግባራትን በግልጽ መመሪያዎችና ምሳሌዎች የማቅረብ ክፍተት ያለበት መሆኑ በድክመት ተነስቷል። በመሆኑም የመጽሀፍ አዘጋጆች በመጽሀፍ ዝግጅት (ማሻሻያ)  ወቅት ለእነዚህ ጉዳዮች ትኩረት ቢሰጡ የተሻለ መጽሀፍ ለማዘጋጀት ይረዳቸዋል።
- **ለጥናት አድራጊዎች፡-** ይህ ጥናት ቅይጥ የምርምር ዘዴን በመከተል በደቡብ ክልል በጉራጌ ዞን በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው አዲሱ የ6ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ምን እንደሚመስል በመገምገም የተከናወነ ነው። የጥናቱ ውጤትም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ በተወሰነ መልኩ ክፍተት እንዳለበት ጠቋሚ ነው። በመሆኑም ተመራማሪዎች በመፅሀፉ የቀረቡ ሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ላይ ማለትም  በስነ ልሳንና በስነ ፅሁፍ ላይ ያተኮሩ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች

አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ላይ እንዲሁም በቃላት ትምህርት አሰጣጥ የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎና የመምህራን የቃላት ትምህርት አተገባበር ላይ ጥናት ቢያደርጉ የተሻለ ይሆናል የሚሉ አስተያየቶች ተሰንዝረዋል፡፡

# ዋቢ ጽሁፎች


ማረው አለሙ፡፡ (2003)፡፡ ዘመናዊ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማርያ ዘዴ፡፡ አዲስ አበባ ፣አልፋ ማተሚያ ቤት፡፡

ምንውየለት ደነቀው፡፡(2005)፡፡ *"በአማራ ክልል በስራ ላይ ያሉት የ7ኛና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማርያ መፅሀፍት የቃላት ትምህርት የይዘት አመራረጥ፣አደረጃጀና አቀራረብ ግምገማ"*፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ለሁለተኛ ዲግሪ ማሙያነት የቀረበ (*ያልታተመ*)፡፡

ሞላ አጽብሃ፡፡ (2003)፡፡ *"በትግራይ ክልል ለስምንተኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቃላት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ትንተና"* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለሁለተኛ ዲግሪ መሚያነት የቀረበ ጥናት (*ያልታተመ*)፡፡

በድሉ ዋቅጅራ፡፡ (1996)፡፡ በስነ-ጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር፡፡ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ባየ ይማም፡፡ (1987)፡፡ *የአማርኛ ሰዋስው*፡፡ አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ድ፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር፡፡ (2004)፡፡ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት *መማሪያ* መጽሀፍ፣ ዘጠነኛ ክፍል፡፡ ዱባይ፣ አል-ጉሬር አታሚና አሳታሚ ድርጅት፡፡

አልማዝ ዮሀንስ፡፡ (2012*)፡፡ "የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ የቃላት አደረጃጀትና አቀራረብ ፍተሻ"፡፡* ጎንደር ዩኒቨርሲቲ፣ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት(*ያልታተመ*)፡፡

እንግዳው ሙለዓለም፡፡ (1993)፡፡ *ቀዳሚው ትውልድ የአማርኛ ሰዋስው*፡፡ አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ (1996)፡፡ *የስነ-ጽሁፍ መሰረታውያን*፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት

የሻው ተሰማ፡፡ (1996)፡፡ *ልሳነ-ብዕር ከመልሳነ ሰብዕ* ፡፡ አዲስ አበባ፣ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡ (2009)፡፡ *የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር፡፡* አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

Dubin, F. and Olshtain, E. (1986). *Course design; Developing programs and Materials for Aanguage Learning,* Cambridge: Cambridge University Press.

Elley, W. (1989). *Tailoring the Evolution to Fit the Context*. In Johnson, R. (ed).

The Second Language Curriculum. Cambridge; Cambridge University Press. Vol.21,No.2, pp.53-60

Gairns, R. and S. Redman. (1986). Working With Words; Aguide to Teaching and Learning Vocabulary. Cambridge:CUP.

Harmer, J. and R. Rossner. (1991). More than Words: Vocabulary for Upper Intermediate to Advanced Student. ESSEX: Longman Group (UK) Ltd.

Hutchinson, T and Torres, E, (1994). "*the Text book as agent of change"* ELT Journal. Vol. 48, No. 4, PP. 315-328.

Lewis, M. (1993). *The Lexical Approach*. London: Comercial Colour Press.

McCarten, J. (2007). Teaching Vocabulary. Cambridge: Cambridge University Press.

McCarthy, M. (1990). Vocabulary. Oxford. Oxford University Press.

Morgan, J. and Rinvolucri, M. (1986). Vocabulary; Oxford: CUP.

Richards, J. C. 2001. *The Context of Language Teaching,* New York: Cambridg University press.

Seal,B.D (1991). V*ocabulary Learning and Teaching*. In M. Celce-Murcia (Ed.), Teaching English as a Second or foreign Language (pp.296-311).

Boston, MA: Heinle & Heinle Publication.

Sheldon, L.E (1987). *ELT Text and Materials: Problem in Evaluating and development*. Oxford: Modern English Publication.

Sheldon, L.E. (1988). *Evaluating ELT Textbooks and Materials. English Language Teaching Journal,* 42(4), pp.237-246.

Ur, Penny ( 2009). *A Course in Language Teaching Practice and Theory*. Cambrdige: Cambridge University Press.

Wallace, M. (1988). *Teaching Vocabulary*. Chicago: University of Chicago Press.

Wilkins, (1972). *Linguistics in Language Teaching*. London, The English language Book Society and Edward Arnold (publishers) Ltd.

# አባሪዎች

## ቃለመጠይቅ

በአዲስ አበባ ዩነቨርሲቲ

የሂውማኒቲ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

## ኣባሪ አንድ

በ2015 ዓ.ም በደቡብ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ስራ ላይ በዋለው አዲሱ የ6ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ላዘጋጁ / ላሻሻሉ ባለሙያዎች የቀረበ ቃለ-መጠይቅ፡፡

ይህ ቃለ መጠይቅ የተዘጋጀው "በ2015 ዓ.ም በደቡብ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ አዲስ በታተመው የ6ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ" በሚል ርዕስ ለሚደረገው የሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን ከዚህ ጥናት መረጃነት በዘለለ ለምንም ነገር የማልጠቀምበት ሲሆን የሚሰጧቸው እያንዳንዱ መረጃዎች ሚስጥራዊነታቸው የተጠበቀ ነው፡፡

ውድ ጊዜዎን ሰውተው ለሚያደርጉልኝ ትብብር ከወዲሁ አመሰግናለሁ፡፡

**ክፍል አንድ፡- የመፅሀፉ አዘጋጆች / አሻሻዮች አጠቃላይ ዳራ**

ቃለ መጠይቁ የተካሄደበት ቀን........ ቦታ …………………….. ሰዓት …....

ፆታ……... ዕድሜ……... የትምህርት ደረጃ ………. የአገልግሎት ዘመን………….

የሰለጠኑበት የትምህርት ዘርፍ አብይ …………………………..

መፅሀፉን ባዘጋጁ / ባሻሻሉ ጊዜ የነበርዎት የስራ ሀላፊነት ………………………

እየሰሩበት ያሉበት ሙያ ………………………………………………

አሁን (2015 ዓ.ም) ያሉበት የትምህርት ደረጃ ……………………………….

ክፍል ሁለት፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች  ትክክል ነው የሚሉትን ሀሳብ እንዲሰጡኝ በትህትና እጠይቃለሁ።

1.በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች የተደራጁት በቃላት ቅርፅ ተመሳስሎ፣ በሚያወሱት ርዕሰ ጉዳይ፣  ወይስ በፍቺ ዝምድናቸው አማካይነት ነው?

2. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘት መልመጃዎች አውድን መሠረት አድርገው የተዘጋጁ ናቸው?

3. በመማሪያ መጽሀፉ የቀረቡት ቃላት ቃላቱ ባላቸው የፍቺ ዝምድና አማካይነት ቀርበዋል? (ከተመሳስሎና ተቃርኖ፤ ከቃላት የማጠቃለልና የመዘርዘር ሁኔታ፤ ከቃላት አብሮ ተሰላፊነት አንጻር)

4. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች በመዝገበ ቃላት ተደግፈው ቀርበዋል?

5. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘት ተግባራት  በግልጽ መመሪያዎችና ምሳሌዎች  የቀረቡ ናቸው ?

6. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት ቃላት ይዘት መልመጃዎች ከሁሉም የቋንቋ ክሂሎች ጋር ግንኙነት ፈጥረው የተዘጋጁ ናቸው?

7. አጠቃላይ ለቃላት ትምህርት ዝግጅቱ የተሰጠውን ትኩረትና ጊዜ እንዴት ይገልፁታል? (የተለየ ትኩረትና ጊዜ ወይስ ለሁሉም ይዘቶች እኩል ትኩረትና ጊዜ ተሰጥቷል)

8. ይህ መማሪያ መፅሀፍ ቀድሞ ከነበረው የመማሪያ መፅሀፍ የቃላት ትምህርት መልመጃዎችን በተመለከተ ምን ያሻሻለው ነገር አለ?

# አባሪ ሁለት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂውማኒቲ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

በ2015 ዓ.ም በደቡብ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ስራ ላይ በዋለው አዲሱ የ6ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ለሚጠቀሙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቀረበ ቃለ-መጠይቅ

ውድ መምህራን፡- ይህ ቃለ መጠይቅ የተዘጋጀው "በ2015 ዓ.ም በደቡብ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ አዲስ በታተመው የ6ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ" በሚል ርዕስ ለሚደረገው የሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን ከዚህ ጥናት መረጃነት በዘለለ ለምንም ነገር የማልጠቀምበት ሲሆን የሚሰጧቸው እያንዳንዱ መረጃዎች ሚስጥራዊነታቸው የተጠበቀ ነው፡፡

ውድ ጊዜዎን ሰውተው ለሚያደርጉልኝ ትብብር ከወዲሁ አመሰግናለሁ፡፡

ክፍል አንድ፡- ቃለ መጠይቅ የቀረበላቸው መምህር 1 መረጃ

1. ቃለ መጠይቁ የተካሄደበት ቀን ………… ቦታ ……….…………..  ሰዓት …....

2. ፆታ……….. 3. ዕድሜ …….. 4. የትምህርት ደረጃ ………..

5. የሰለጠኑበት የትምህርት ዘርፍ አብይ ………. ንዑስ ……….

6. የአገልግሎት ዘመን ………….

ክፍል ሁለት፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃለ-መጠይቆች ትክክል ነው የሚሉትን ሀሳብ እንዲሰጡን በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

1. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች የቃላት ቅርጽን፣ አንድን ርዕሰ ጉዳይ እንዲሁም የተለያዩ ፍቺዎችን መሰረት አድርገው የተደራጁ ናቸው ብለው ያስባሉ? ሀሳብዎን አብራርተው ይግለፁ፡፡

አዎ አስባለሁ፤ ምክንያቱም በመጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት ቃላት በእነዚህ መንገዶች የተደራጁ ናቸው፡፡ ለምሳሌ የፈሊጣዊ ቃላት፣ የእማሬያዊና ፍካሬዊ ቃላት እንዲሁም አውዳዊ ቃላትን ፍቺ ብንመለከት የተለያዩ የቃላት ፍቺን መሰረት አድርገው የተዘጋጁ ናቸው፡፡

2. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት መልመጃዎች አውድን መሠረት አድርገው የቀረቡ ናቸው ብለው ያስባሉ?

አዎ አስባለሁ፤ ምክንያቱም በመጽሀፉ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች አውድን መሰረት ያደረጉ የቃላት ትምህርት ይዘቶች ቀርበዋል፡፡

3. በመማሪያ መጽሀፉ የቀረቡት ቃላት ቃላቱ ባላቸው የፍቺ ዝምድና አማካይነት ቀርበዋል? ማለትም (በተመሳስሎና ተቃርኖ፤ በቃላት የማጠቃለልና የመዘርዘር ሁኔታ፤ ከቃላት አብሮ ተሰላፊነት አንጻር)

በመማሪያ መጽሀፉ የቀረቡት ቃላት በአብዛኛው በፍቺ ዝምድናቸው አማካይነት ነው፡፡ በማጠቃለልና በመዘርዘር ሁኔታ የቀረቡ ቃላት እስካሁን አላጋጠሙኝም በተመሳስሎና በተቃርኖ የቀረቡ ቃላት ግን በርካታ ናቸው፡፡

4. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች በመዝገበ ቃላት ተደግፈው ቀርበዋል ብለው ያስባሉ?

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በመዝገበ ቃላት ተደግፈው የቀረቡት ቃለት ቢኖሩም በቁጥር ውስን ናቸው ፡፡

5. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘት ተግባራት በግልጽ መመሪያዎችና ምሳሌዎች የቀረቡ ናቸው ብለው ያስባሉ?

በመማሪያ መጽሀፉ የቀረቡት አብዛኛዎቹ የቃላት ትምህርት ይዘት ተግባራት በግልጽ መመሪያዎች የቀረቡ ናቸው፡፡ ምሳሌን በተመለከተ አንዳንድ ቦታ ላይ ብቻ ነው የተሰጠው፡፡

6. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት ቃላት ይዘት መልመጃዎች ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር ያላቸው ግንኙነት ፈጥረው የተዘጋጁ ናቸው?

በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ይዘት መልመጃዎች ራሳቸውን ችለው ከመቅረባቸው ባሻገር ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅተው በተለያ ቦታዎች ላይ የቀረቡ ናቸው፡፡

# አባሪ ሶስት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂውማኒቲ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

በ2015 ዓ.ም በደቡብ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ስራ ላይ በዋለው አዲሱ የ6ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ለሚጠቀሙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቀረበ ቃለ-መጠይቅ

ውድ መምህራን፡- ይህ ቃለ መጠይቅ የተዘጋጀው "በ2015 ዓ.ም በደቡብ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ አዲስ በታተመው የ6ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ" በሚል ርዕስ ለሚደረገው የሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን ከዚህ ጥናት መረጃነት በዘለለ ለምንም ነገር የማልጠቀምበት ሲሆን የሚሰጧቸው እያንዳንዱ መረጃዎች ሚስጥራዊነታቸው የተጠበቀ ነው።

ውድ ጊዜዎን ሰውተው ለሚያደርጉልኝ ትብብር ከወዲሁ አመሰግናለሁ።

ክፍል አንድ፡- ቃለ መጠይቅ የቀረበላቸው መምህር 2 መረጃ

1. ቃለ መጠይቁ የተካሄደበት ቀን ………… ቦታ ……….…………. ሰዓት …....

2. ፆታ……….. 3. ዕድሜ …….. 4. የትምህርት ደረጃ ………..

5. የሰለጠኑበት የትምህርት ዘርፍ አብይ ………. ንዑስ ……….

6. የአገልግሎት ዘመን ………….

ክፍል ሁለት፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃለ-መጠይቆች ትክክል ነው የሚሉትን ሀሳብ እንዲሰጡን በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

1. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች የቃላት ቅርጽን፣ አንድን ርዕሰ ጉዳይ እንዲሁም የተለያዩ ፍቺዎችን መሰረት አድርገው የተደራጁ ናቸው ብለው ያስባሉ? ሀሳብዎን አብራርተው ይግለፁ፡፡

አብዛኛዎቹ ይዘቶች ከላይ የተዘረሩትን መስፈርቶች መሰረት አድርገው የተዘጋጁ ናቸው፡፡

2. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት መልመጃዎች አውድን መሠረት አድርገው የቀረቡ ናቸው ብለው ያስባሉ?

በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ከቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች ውስጥ አንዳንዶቹ አውዳዊ አቀራረብን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡

3. በመማሪያ መጽሀፉ የቀረቡት ቃላት ቃላቱ ባላቸው የፍቺ ዝምድና አማካይነት ቀርበዋል? ማለትም (በተመሳስሎና ተቃርኖ፤ በቃላት የማጠቃለልና የመዘርዘር ሁኔታ፤ ከቃላት አብሮ ተሰላፊነት አንጻር)

አዎ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት ቃላት በፍቺ ዝምድናቸው የቀረቡ ናቸው

4. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች በመዝገበ ቃላት ተደግፈው ቀርበዋል ብለው ያስባሉ?

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በመዝገበ ቃላት ተደግፈው የቀረቡት ቃለት ቢኖሩም በቁጥር ውስን ናቸው ፡፡

5. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘት ተግባራት በግልጽ መመሪያዎችና ምሳሌዎች የቀረቡ ናቸው ብለው ያስባሉ?

በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘት ተግባራት በግልጽ መመሪያዎች የቀረቡ መሆናቸውንና በቂ ምሳሌዎች ያልተሰጣቸ ናቸው፡፡

6. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት ቃላት ይዘት መልመጃዎች ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር ያላቸው ግንኙነት ፈጥረው የተዘጋጁ ናቸው?

በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ይዘት መልመጃዎች ራሳቸውን ችለው ከመቅረባቸው ባሻገር ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅተው በተለያ ቦታዎች ላይ የቀረቡ ናቸው፡፡

## አባሪ አራት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂውማኒቲ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

በ2015 ዓ.ም በደቡብ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ስራ ላይ በዋለው አዲሱ የ6ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ለሚጠቀሙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቀረበ ቃለ-መጠይቅ

ውድ መምህራን፦ ይህ ቃለ መጠይቅ የተዘጋጀው "በ2015 ዓ.ም በደቡብ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ አዲስ በታተመው የ6ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ" በሚል ርዕስ ለሚደረገው የሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን ከዚህ ጥናት መረጃነት በዘለለ ለምንም ነገር የማልጠቀምበት ሲሆን የሚሰጧቸው እያንዳንዱ መረጃዎች ሚስጥራዊነታቸው የተጠበቀ ነው፡፡

ውድ ጊዜዎን ሰውተው ለሚያደርጉልኝ ትብብር ከወዲሁ አመሰግናለሁ፡፡

ክፍል አንድ፦ ቃለ መጠይቅ የቀረበላቸው መምህር 3 መረጃ

1. ቃለ መጠይቁ የተካሄደበት ቀን ………… ቦታ ……….…………..  ሰዓት ….....

2. ፆታ……….. 3. ዕድሜ …….. 4. የትምህርት ደረጃ ………..

5. የሰለጠኑበት የትምህርት ዘርፍ አብይ ………. ንዑስ ……….

6. የአገልግሎት ዘመን ………….

ክፍል ሁለት፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃለ-መጠይቆች ትክክል ነው የሚሉትን ሀሳብ እንዲሰጡን በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

1. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች የቃላት ቅርጽን፣ አንድን ርዕሰ ጉዳይ እንዲሁም የተለያዩ ፍቺዎችን መሰረት አድርገው የተደራጁ ናቸው ብለው ያስባሉ? ሀሳብዎን አብራርተው ይግለፁ፡፡

አዎ አስባለሁ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች የቃላት ቅርጽን፣ አንድን ርዕሰ ጉዳይ እንዲሁም የተለያዩ ፍቺዎችን መሰረት አድርገው የተደራጁ ናቸው፡፡

2. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት መልመጃዎች አውድን መሠረት አድርገው የቀረቡ ናቸው ብለው ያስባሉ?

አዎ አስባለሁ፤ ምክንያቱም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ በርካታ ቦታዎች ላይ አውዳዊ አቀራረብን መሰረት ያደረጉ የቃላት ትምህርት ይዘቶች ቀርበዋል

3. በመማሪያ መጽሀፉ የቀረቡት ቃላት ቃላቱ ባላቸው የፍቺ ዝምድና አማካይነት ቀርበዋል? ማለትም (በተመሳስሎና ተቃርኖ፤ በቃላት የማጠቃለልና የመዘርዘር ሁኔታ፤ ከቃላት አብሮ ተሰላፊነት አንጻር)

አዎ አብዛኛው ቃላት የቀረቡት በፍቺ ዝምድናቸው ነው፡፡

4. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች በመዝገበ ቃላት ተደግፈው ቀርበዋል ብለው ያስባሉ?

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በመዝገበ ቃላት ተደግፈው የቀረቡት ቃለት ቢኖሩም በቁጥር ውስን ናቸው

5. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘት ተግባራት በግልጽ መመሪያዎችና ምሳሌዎች የቀረቡ ናቸው ብለው ያስባሉ?

በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘት ተግባራት በግልጽ መመሪያዎች የቀረቡ መሆናቸውንና በቂ ምሳሌዎች ያልተሰጣቸ ናቸው፡፡

6. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት ቃላት ይዘት መልመጃዎች ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር ያላቸው ግንኙነት ፈጥረው የተዘጋጁ ናቸው?

በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ይዘት መልመጃዎች ራሳቸውን ችለው ከመቅረባቸው ባሻገር ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅተው በተለያ ቦታዎች ላይ የቀረቡ ናቸው፡፡

# ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜንና ፊርማዬን ያስቀመጥኩት በተግባራዊ ስነ-ልሳን አማርኛን ለማስተማር የድህረ-ምረቃ ተማሪ ስሆን ይህ ጥናት የራሴ ስራ መሆኑንና በስራው ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ምንጮች በሙሉ በዋቢ መፅሀፍት ላይ የጠቀስኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም -------------------------------------

ፊርማ -------------------------------------

የማስረከቢያ ቀን --------------------------------------